# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት



## በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የኢንዱስትሪ ዝቃጭ/ቆሻሻ/ አወጋገድ ሥርዓት ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት



የካቲት 2011 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

# ማውጫ


## ክፍል አንድ

**መግቢያ ........................................................................................................ 1**

የኮሚሽኑ ተልዕኮ ........................................................................................................ 2

የኮሚሽኑ ራዕይ ........................................................................................................ 3

የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባራት ........................................................................................................ 3

የኮሚሽኑ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል አደረጃጀት ........................................................................................................ 5

የፋይናንስ ምንጭ ........................................................................................................ 6

በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የአሰራር ሂደት መግለጫ........................................................................................................ 7

የኦዲቱ አላማ ........................................................................................................ 8

የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ........................................................................................................ 8

የኦዲት መመዘኛ መስፈርት ........................................................................................................ 9

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ........................................................................................................ 9

## ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

*ሀ.* **በመ/ቤቱ የኢንዱስትሪ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ ፖሊሲዎች፣ አዋጆችና ደንቦች እንዲሁም የማስፈፀሚያ መመሪያዎች፣ ማኑዋሎችና ደረጃዎች መዘጋጀታቸውን እና ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ፣ ........................................................................................................ 10**

በኮሚሽኑ የአካባቢ ብክለትን ለመቆጣጠር የወጡ አዋጆች
ደንብና መመሪያ መውጣታቱንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤........................................................................................................ 10

በወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ ግንዛቤ ማስጨበጫ
መሰጠቱንና ለተጠቃሚው ተደራሽ ማድረጉን በተመለከተ፤........................................................................................................ 14

በኮሚሽኑ ለኢንዱስትሪ ዝቃጭ/ቆሻሻ

የሚያገለግሉ ደረጃዎች መውጣታቸውን በተመለከተ፤ ....... 16

ወደ ውሃ አካላት እና ወደ ፍሳሽ መቀበያ መስመሮች
የሚለቀቁ ፍሳሾችን ደረጃ መውጣቱን በተመለከተ፤ ....... 20

ፋብሪካዎች ወደ ሥራ ከመግባታቸው በፊት የአካባቢ ተጽዕኖ
ግምገማ ሰነድ ማቅረባቸውንና ሰነዱን ተግባራዊ ማድረጋቸውን በተመለከተ፤ ....... 30

የዝቃጭ ማስወገጃ ወይም ማከሚያ ግንባታዎች በአካባቢ ተጽዕኖ
ግምገማ ተቀባይነት ያለውን ደረጃ ተከትለው መሰራታቸውን በተመለከተ፤ ....... 35

ለ. በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ለሚወገዱ የኢንዱስትሪ ዝቃጭ/ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ ደረጃውን የጠበቀ ስለመሆኑ የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤ **....... 37**

በኮሚሽኑ የአካባቢ ብክለት በተመለከተ የወጡ ህጐች
ስለመተግበራቸው የተጠናከረ የክትትል ስርዓት መኖሩን በተመለከተ፤ **....... 37**

ፋብሪካዎች በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለማስተካከል ....... 41

እና ችግሮችን ለመፍታት እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ፤ ....... 41

ኮሚሽኑ ኢንዱስትሪ /ዝቃጮች/ ቆሻሻዎች አወጋገድ ችግሮች ....... 45

እና መፍትሔዎች ላይ ጥናት ማጥናቱን በተመለከተ፤ ....... 45

ኮሚሽነሩ ፋብሪካዎች የአካባቢ አያያዝ መቆጣጠሪያ ዘዴ/ሥርዓት መኖሩ ....... 46

እና የአካባቢ የውስጥ ኦዲት ማስደረጋቸውን ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤ ....... 46

ሐ. መ/ቤቱ ከኢንዱስትሪ ዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ ጋር በተያያዘ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን፣ እንዲሁም የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤ **....... 49**

ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ....... 49

ጠንካራ የሆነ ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን በተመለከተ፤ ....... 49

ኮሚሽኑ የተቀላጠፈ የመረጃ አያያዝና ....... 51

አጠቃቀም ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ፤ ....... 51

ፋብሪካዎች ያመነጩቱን በካይ ነገር ያስወገዱበትን መንገድ መረጃ መያዛቸውንና ኮሚሽኑ በኢትዮጵያ የበካይ ነገሮች መጠንን አወጋገድ ዘገባ ማቅረቡን በተመለከተ፤ ....... 52

**ክፍል ሦስት** ........................................................................ **53**

*መደመደሚያ* ........................................................................ **53**

**ክፍል አራት** ........................................................................ **57**

የማሻሻያ ሐሳቦች ........................................................................ **57**

## አባሪ አንድ ........................................................................ I

የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ........................................................................ I

## አባሪ ሁለት

የፋብሪካዎች የፍሳሽ ቆሻሻ ደረጃዎች STANDARDS ........................... VI

# ዋና ዋና ግኝቶች ማጠቃለያ (Executive Summery)

የተመረጠው የኦዲት አካባቢ የኢንዱስት ዝቃጭ/ቆሻሻ/ አወጋገድ ሥርዓት ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ ሲሆን የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የልማት አጋዥ የሆኑ የማምረቻ ተቋማት የአካባቢ ህጎችንና ደረጃዎችን በማክበር በየትኛውም አካባቢ የሚኖሩ የሀገራችን ዜጎች በጤናና በኑሮ ሁኔታ ላይ ጉዳት ከሚያደርሱ የፋብሪካ ብክለቶች ነጻ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የሚደጋገፍና የሚናበብ አሰራር መኖሩን፣ ሊለኩ ሊዘገቡና ሊረጋገጡ በሚችሉ መስፈርቶች መሰረት ያደረገ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት መኖሩን በመገምገም የተገኘዉን ጠንካራ ጎን በማበረታታትና ድክመቶችን በመለየት የአምራች ድርጅቶች የአካባቢ ብክለትን ለማስቀረት የሚደረገው የሥራ እንቅስቃሴ ቀጣይነት ያለውና አስተማማኝ ስርዓት በመዘርጋት በተሻለ ብቃት የሚወጣበትን አቅም እንዲፈጥር የማሻሻያ ሀሳብ ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡ በዚህ መሠረት በኦዲቱ የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 እና የአካባቢ ብክለት ቁጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 ከወጡ የቆዩና የፋብሪካ ቴክኖሎጂ እያደገ እና የኢንዱስትሪዎች ምርት እየጨመረ እንደመምጣቱ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ያለቸው ክፍተቶች ታይቶ አለመሻሻላቸው የአካባቢ ብክለትን ለመቀነስ በሚደረገው ሂደት ላይ ክፍተት መፍጠሩ፣
- የኢንዱስትሪን ብክለት ለመከላከል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 159/2001 ላይ የተዘረዘሩ ግዴታዎችን ያላከበሩ ፋብሪካዎች ላይ በተጠቀሰው ደንብ አንቀጽ 7 ቁጥር 1 እና 2 እንዲሁም አንቀጽ 12 መሰረት እርምጃ ለመውሰድ (ለምሳሌ ፋብሪካዎችን ፍቃድ ለመሰረዝ፣ ለማገድና ወደ ሌላ ቦታ ለማዘዋወር ወዘተ) መውጣት የሚገባቸው የአፈፃፀም መመሪያዎች አለመውጣቱ፣
- ለኢንዱስትሪ የቆሻሻ ዓይነቶች አመነጫጨት፣ አያያዝ፣ አከመቻቸት፣ አመካከን፣ አጓጓዝ እና አወጋገድ የሚያገለግሉ የመጠን እና የአተገባበር ደረጃዎች አለመውጣቱ ለማሳያ ያህል፡-(ቆሻሻ ማከሚያ (Sedimentation tank) የሚወጣ የፍሳሽ ቅሪት (Sludge Cake))፣
- ከፋብሪካዎች የሚወጡ ወደ ውሃ አካላትና ወደ ፍሳሽ መቀበያ መስመሮች የሚለቀቁ ፍሳሾችን በተመለከተ አገር አቀፍ ደረጃ ያለ ቢሆንም በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት ፋብሪካዎች ውስጥ፡-
  - በሞጆ በናሙና ከታዩት 14 ቆዳ ፋብሪካዎች ውስጥ 10 ፋብሪካዎች የመጀመሪያ ደረጃ የፍሳሽ ማከምያ መሳሪያዎች ብቻ ያላቸው ሲሆን በተቀሩት አራቱ (ዲኤክስ፣ ፈሪዳ፣ ጆርጅ ሹ፣ ዩናይትድ ቫዚን) ቆዳ ፋብሪካዎች 2ኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ ያላቸው ቢሆንም 3ኛ የፍሳሽ ማከሚያ ባለመኖራቸው ምክንያት የብክለት መጠናቸው ቢለያይም ሁሉም ደረጃውን

ያልጠበቀ  ፍሳሽ ወደ ሞጆ ወንዝ የሚለቁ በሞጆ ወንዝ ላይ ከፍተኛ ብክለት እያደረሱ መሆኑ፣

- በሰበታ ከተማ በናሙና ከታዩት 7 ፋብሪካዎች አራቱ (ባለዛፍ እና ብሔራዊ አረቄ ፋብሪካ፣ ጂዶንግ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ አይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ) ወደ ሀጠበላ ወንዝ እና ወደ ፍሳሽ መስመር የተበከለ ውሃ የሚለቁ መሆናቸው፣
- በአዲስ አበባ ከ7 ቆዳ ፋብሪካዎች ውስጥ ስድስቱ የቆዳ ፋብሪካዎች 1ኛ ደረጃ የፍሳሽ ማከሚያ ብቻ ያላቸው በመሆኑና አንዱ 2ኛ ደረጃ የፍሳሽ ማከሚያ ያለው ሲሆን ይርጋለም ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ የፍሳሽ ማጣሪያ ባለመኖሩ ምክንያት በተጨማሪም በአዲስ አበባ ያሉ ትልልቅ ፋብሪካዎች ያለምንም የፍሳሽ ማጣሪያ ከተፈቀደው የልቀት ደረጃ በላይ የሚለቁ በመሆናቸው ደረጃውን ያልጠበቀ ፍሳሽ ላይኛውና ታችኛው የአቃቂ ገባር ወንዞች እየበከሉ መሆናቸው፣
- በኮምቦልቻ ከተማ ሁሃክሱ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ እና በቱሁሌደሬ ወረዳ ኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ (ሐይቅ) 1ኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ ብቻ ያላቸው በመሆኑ፣ ኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሦስት ሼዶች ላይ ሙሉ ለሙሉ ሥራ የጀመረ ቢሆንም የተገነባው ማጣሪያ ሥራውን ባለመጀመሩ እና ደሴ ቁራ ፋብሪካ  የፍሳሽ ማጣሪያ ቴክኖሎጂ ባለመኖሩ፣ ኢትዮ ቆዳ ፋብሪካ በሎሚ ወረዳ (ኤጀርሳ) ሁለተኛ ደረጃ ቢኖረውም ሦስተኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ የሌለው በመሆኑና ሁሉም ደረጃውን ያልጠበቀ/ያልተጣራ ፍሳሽ አብዛኞቹ ወደ ቦርከና፣ ኢዮሌ እና የመሳሰሉት ወንዞች የሚለቁ በመሆናቸው በወንዛቹ ላይ ብክለት እያደረሱ መሆኑ፣
- በተመሳሳይ ባህርዳር ከተማ አማራ ፓይፕ የፍሳሽ ማጣሪያ ባለመኖሩ፣ ሀበሻ ቆዳ ፋብሪካ የመጀመሪያ ደረጃ ብቻ በመኖሩ እና ባህርዳር ጨርቃ ጨርቅና እና ኮካኮላ ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ ሁለተኛ ደረጃ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መሳሪያው የሚሰራ ቢሆንም ከማጣሪያ መሳሪያው በቀጥታ ወደ ማስወገጃ ቱቦ በማያያዝ አልፎ አልፎ በሚለቀቅ ያልተጣራ ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ውጭ በመልቀቅ ብክለት እያደረሱ መሆናቸው እና ከላይ የተጠቀሱት አብዛኛው ወንዞች የአዋሽ ገባር ወንዞች በመሆናቸው ወንዙ ላይ ከፍተኛ ብክለት እያደረሱ መሆኑ፣ እንዲሁም የፍሳሽ ማጣሪያ ያላቸው ፋብሪካዎችም ቢሆንም ጊዜ ጠብቀው ሌሊት እና መብራት በሚጠፋበት ወቅት ያልታከመ ውሃ የሚለቁ መሆኑ፣ አብዛኛው ፋብሪካዎች ቤተ-ሙከራ የሌላቸውና ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚለቁት ፍሳሽ ደረጃውን የጠበቀ ስለመሆኑ በቤተ-ሙከራ የማያስመረምሩ መሆኑ፣

➲ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 መሰረት ማንኛውም ፍቃድ (ኢንቨስትመንት፣ የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ) ሰጪ መሥሪያ ቤት ፍቃድ ከመሥጠቱ በፊት

ከኮሚሽኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንዲሆን የይሁንታ ፍቃድ እንዲያቀርብ መደረጉን በተመለከተ፡-

- በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልል ኢንቨስትመን ቢሮ፣ ሞጆ፣ አዳማ፣ በባህርዳር፣ ደሴ፣ ኮምልቻ እና ደቡብ ወሎ ዞን ኢንቨስትመንት ቢሮዎች ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፍቃድ ሲወስዱ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ የይሁንታ ፍቃድ እንዲያቀርቡ የማይደረግ መሆኑ፣
- በተመሳሳይ በናሙና በታዩት በሁሉም ንግድ/ሥራ ፍቃድ ሰጪ ተቋማት(ንግድ ሚኒስቴር፣ የአማራ፣ የኦሮሚያ፣ ሞጆ፣ ኮምቦልቻ፣ ባህርዳርና አዲስ አበባ የንግድ ቢሮዎች) ለባለሀብቶች የንግድ ፍቃድ ወይም የሥራ የንግድ ፍቃድ ሲሰጡ ከሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት የይሁንታ ፍቃድ/የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ እንዲያቀርቡ የማይደረግ መሆኑ፣

- በተጨማሪም የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 159/2001 መሰረት ለማምረቻ ተቋማት የሥራ ፈቃድ ሲሰጡ ልቀቱ በካይ አለመሆኑን፣ ከሆነም በአካባቢ ደረጃ ከተፈቀደው ጣራ የማይበልጥ እና ልቀቱ ወደ አካባቢ ቢለቀቅ አደጋ የማያስከትል መሆኑን የማረጋገጥ ሥራ የማይሰሩ መሆናቸው፣
- በናሙና በታዩት በሁሉም ክልሎች፣ ከተሞች፣ ዞንና ወረዳዎች የመንግሥት ፕሮጀክቶች /ኢንዱስትሪ ፓርኮችን/ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሳያሰሩ ወደ ሥራ የገቡ መሆናቸው፣
- የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ/የአካባቢ አያያዝ እቅድ ያላቸው በናሙና ከታዩት አብዛኛው ፋብሪካዎች ሰነዱን በፋብሪካቸው የማይገኝና ተግባራዊ የማያደርጉ መኖራቸው፣
- በሚንስትሮች ምክር ቤት ህንጻ ደንብ ቁጥር 243/2003 መሰረት በኢንዱስትሪዎች የሚገነባ የዝቃጭ ማስወገጃ ወይም ማከሚያ ግንባታ በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ መሠረትና ተቀባይነት ያለውን ደረጃ ተከትሎ የተሰራ ስለመሆኑ የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩ፣
- የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የአካባቢ ብክለት በተመለከተ ሁሉንም ተደራሽ ከማድረግና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመከታተል ያለው የክትትል ስርዓት ጠንካራ አለመሆኑ ማለትም፡-
  - የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የአካባቢ ብክለትን ለመከታተል በሚያስችል መልኩ በሰው ኃይል በተገቢ ሁኔታ ያልተደራጁ መሆኑ፣
  - እንዲሁም ከከተማ ራቅ ብለው የሚገኙ ፋብሪካዎች ወጥ በሆነ መልኩ ለመከታተል የተሽከርካሪ እጥረት መኖሩ፣
  - በክትትል ወቅት መረጃ ለመያዝ የሚያስችል ካሜራ፣ ፋብሪካው ያለበትን ቦታ ለማወቅ ጂ.ፒ.ኤ.ስ፣ የቢሮ መገልገያ ግብዓት የሌላቸው (ኮምቦልቻ፣ ሞጆ ከተሞችና ሎሜ ወረዳ) የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በመኖራቸው የክትትል መረጃዎች በተደራጀ መልኩ ለመያዝ አለመቻሉ፣

- ከከተማ ራቅ ያሉ ፋብሪካዎችን ቀጣይ በሆነ መልኩ ለመከታተል ያመች ዘንድ ሥራው እታችኛው መዋቅር ድረስ ያልተዘረጋ እና ለክትትል በሚያመች መልኩ ወጥ እና ተነባቢ የሆነ አደረጃጀት አለመኖሩ፣
- በፌዴራል ደረጃ ኮሚሽኑ በ2009 ዓ.ም. 20 እና በ2010 ዓ.ም 30 ፋብሪካዎች፣ አዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት እቅድ መሰረት አድርጐ ክትትል ያደረገባቸው 10 ፋብሪካዎችብቻ፣ በኮምቦልቻ ጥቆማ ሲመጣ ብቻ ክትትል የሚያደርጉ መሆኑ፣

- ከላይ የታዩት ፋብሪካዎች ከ2007 ዓ.ም. ጀምሮ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸውና የብክለት መጠናቸው እየቀነሰ ያልመጣ ቢሆንም ከማስጠንቀቂያ በዘለለ እስከ ሰኔ ወር 2010 ዓ.ም ድረስ ምንም አይነት እርምጃ አለመወሰዱ፣
- የኢንድስትሪ ዝቃጭ በሰው ጤናና በእንስሳት ላይ ያደረሱትን ጉዳት አስመልክቶ በተጨባጭ ስለአደረሱት ወይም ሊያደርሱት ስለሚችሉት ጉዳት መጠን የተጠና ጥናት አለመኖሩ፣
- በናሙና ከታዩት 42 ፋብሪካዎች ውስጥ የአካባቢ አያያዝ መቆጣጠሪያ ዘዴ/ሥርዓት (በጀት መመደብ፣ ፖሊሲ፣ አሃድ፣ የአካባቢ ባለሙያ መቅጠር፣ የአካባቢ አያያዝ እቅድ በማቀድ ወደ ተግባር መግባት ወዘተ) የዘረጉት 10 (24%) ፋብሪካዎች ብቻ ሲሆኑ የተቀሩት 32ቱ /76% / የአካባቢ የአያያዝ ሥርዓት ባለሞያ (የአካባቢ ባለሙያ) የሌላቸው ወይም በከፊል ያላቸው መሆኑ፣
- በናሙና ከታዩት ፋብሪካዎች ውስጥ “ISO” ሰርተፊኬት ለማግኘት ኦዲት ከሚያስደርጉ ጥቂት ፋብሪካዎች (ማለትም ኢትዮ ቆዳ ፋብሪካ፣ ቢ.ጂ.አይ ቢራ ፋብሪካ፣ ኮካኮላ ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ) በስተቀር የተቀሩት ፋብሪካዎች ኦዲት የማያስደርጉ መሆኑ፣
- ከኢንዱስትሪ ዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ ጋር በተያያዘ ኮሚሽኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ የሆነ ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖሩ እንዲሁም ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር የጋራ እቅድ ቢኖርም በእቅድ መሰረት እየተሰራ አለመሆኑ፣
- በኮሚሽኑ በፌዴራል ደረጃ የሚከፈቱ ኢንዱስትሪዎች /አምራች ተቋማት/ ለክትትል በሚያመች መልኩ የተሟላ መረጃ አለመኖሩና የአካባቢ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ለማደራጀትና እና መረጃዎችን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችል የአካባቢ መረጃ ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣

የሚሉ ናቸው፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. የሰው ልጅ  አካባቢን ለህይወቱ መቃናት እና ለተሻለ የኑሮ ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ የሚጠቀምና በመጠቀም ላይ ያለ በመሆኑ በዓለም ላይ አካባቢን ለሚጎዱ/ለሚበክሉ በርካታ የብክለት ምንጮች መንስኤ ሲሆን ቆይቷል፤ መንስኤ በመሆን ላይም ይገኛል፡፡በሰው ልጅ እንቅስቃሴ ውስጥ አካባቢን በእጅጉ ከሚበክሉ ዘርፎች አንዱና ዋንኛው ደግሞ የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፉ ተጠቃሽ ነው፡፡ዘርፉ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያደገ ያለ በመሆኑ ተገቢ ክትትልና ቁጥጥር ካልተደረገበት የሚያደርሰው የብክለት መጠን እየሰፋ እንደሚሄድ ይገመታል፡፡የማምረቻ ተቋማት የምርት ሂደት አካባቢያዊ ዘላቂነት እና ማህበራዊ ተቀባይነት ከሌለው በዘርፉ የተጀመረው ልማት ሊቀለብስ የሚችል ነው፡፡ በመሆኑም የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የብክለትና ብክነት የመከላከያ ወይም የማስወገጃ እርምጃዎች በመውሰድ በልማት ሂደቱ የሚከሰትውን  ብክለት መቀነስ መቻል ይኖርበታል፡፡

2. መንግስት የዜጎችን ሕገ መንግስታዊ የአካባቢ ደህንነት መብት ለማስከበር እና የአካባቢ ጥበቃ ዓላማዎችን ከግብ ለማድረስ ልዩ ልዩ የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ፖሊሲና ሕግጋቶችን አውጥቶ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

3. በአገራችን ህገ መንግሥት አንቀጽ 43 (የልማት መብት)፣ አንቀጽ 44 (የአካባቢ ደህንነት መብት) እና አንቀጽ 92 (የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች) የሚሉ ጠቃሚ ድንጋጌዎችን አካቶ ይገኛል፡፡ የተለያዩ የአካባቢ አዋጆች የአካባቢ ብክለት ቁጥር አዋጅ 300/1995፣ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ ቁጥር 513/1999፣ የኢትዮጵያ የአካባቢ እና የደን ፖሊሲ እና አለም አቀፍ የአካባቢያ የደን ስምምነቶች ፀድቀዋል፡፡ እንዲሁም ማንኛውም ሥራ ወይም ኘሮጀክት ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት በአካባቢ እና በማህበረሰብ ላይ ሊያደርስ የሚችለውን አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተፅእኖ በመለየት አሉታዊ የሆኑትን በመቀነስ ከተቻለም ለማሥቀረት እንዲያስችልም የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ (Environnemental Impact Assesement) ጥናት እንዲያዘጋጅ  የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 ወጥቷል፡፡

4. በተጨማሪም በሀገራችን ከ2001 ዓ.ም. በፊት አብዛኞዎቹ ኢንዱስትሪዎች ብክለትን ለመቀነስና ለመከላከል የሚያስችል አቅም የገነቡበት ሁኔታ ስላልነበር ኢንዱስትሪዎቹ አቅማቸውን በሂደት አጎልብተው የኢንዱስትሪ ብክለትን ለመከላከል የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 159/2001 በማውጣት ኢንዱስትሪዎች የደንቡን ድንጋጌዎች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲያደርጉ የ5 ዓመታት የጊዜ ገደብ ተሰጥቷቸዋል፡፡ በዚህ መሰረት የጊዜ ገደቡ እስኪጠናቀቅ የአካባቢ አያያዝ ዕቅድ አዘጋጅተው እንዲተገብሩና የአካባቢ አያያዝ ኦዲት እንዲያደርጉ ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡

5. የማምረቻ ተቋማት የልማት እንቅስቃሴን ተከትሎ አካባቢን በመጠበቅና ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን በመወጣት የአካባቢ ብክነትና ብክለትን ለማስቀረት ወይም የሚያመነጩትን በካይ አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው ደረጃ የማስወገድ አፈፃፀማቸው በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን ካሉ ተቋማት በፍሳሽ በብናኝ፣ በጋዝ ወይም በጠጣር መልክ የሚያመነጩት በካይ ቆሻሻ አካባቢያዊ ተቀባይነት በሌለው ሁኔታ በቀጥታ በመልቀቅ እያስወገዱ ያሉ ማምረቻ ተቋማት እንዳሉ ከተለያዩ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

6. ይህ ደግሞ የተፈጥሮ ሀብት መሰረት የሆኑትን የአካባቢ ሃብቶች አቅም ይጎዳል፡፡ የጉዳቱ መጠን ከፍ ሲልም ተፈጥሮ ወደ ነበረበት በማይመለስበት ሁኔታ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በሰዎችና በእንስሳት ጤና ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያስከትላል፡፡ ስለሆነም የህዝብ ጤናና የተፈጥሮ ሃብት ሚዛን ተጠብቆ እንዲቆይ፣ ከኢንዱስትሪ የሚመነጭን ቆሻሻ ወይም ተረፈ ምርት መጠን መቀነስ፣ መልሶ መጠቀም፣ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ጠቀሜታ ላይ ለማዋል የማንችለውን ደግሞ አካባቢያዊ ተቀባይነት ባለው ዘዴ ማስወገድ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## የኮሚሽኑ ተልዕኮ

7. የአካባቢና የደን ሃብት አያያዝ፣ ልማትና አጠቃቀም ለዘላቂ ልማትና ለድህነት ቅነሳ አስተዋፅኦ የሚያደረግ ስርዓትን የማዘጋጀትና ተፈጻሚነቱን የማረጋገጥ፣ ምርምርና የቴክኖሎጂ ሽግግርን የማስተባበርና የማካሄድ፣ ትምህርትና ግንዛቤን የመስጠት፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን የማስተባበር፣ የትግባራዎችን አቅም የመገንባት፣ የደን ኢንቨስትመንትና ግብይትን የማስፋፋት፣ ዓለም ዓቀፋዊ የአካባቢና የደን ስምምነቶች ትግበራን የመምራትና የመከታተል እና

ወቅታዊ የአካባቢና የደን ሁኔታ መረጃን የማደራጀት እና ዘገባን የማዘጋጀት ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## የኮሚሽኑ ራዕይ

8. ዘላቂ የአካባቢና የደን አያያዝ፣ ልማትና አጠቃቀምን በማረጋገጥ በ2017 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን የገነባች መካከለኛ ገቢ ያላት ሀገር ሆና ማየት፣

## የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባራት

9. ኮሚሽኑ በአዋጅ ቁጥር 916/2008 መሰረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ተሰጥቶታል፡-

- በሕገ መንግሥቱ የተደነገጉት የአካባቢ ደህንነት ዓላማዎችና በአገሪቱ የአካባቢ ፖሊሲ የተመለከቱት መሠረታዊ መርሆዎች ከግብ መድረሳቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራትን ያስተባብራል፤
- በመንግሥትም ሆነ በግል የሚወጠኑ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ የልማት ፖሊሲዎች፣ ሥልቶች፣ ሕጎች መርሐ ግብሮች እና ፕሮጀክቶች ላይ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ወይም ስልታዊ የአካባቢ ግምገማ ለማካሄድ የሚያስችል ሥርዓት ይዘረጋል፤ ሥርዓቱ በተግባር ላይ መዋሉንም ይከታተላል፤
- ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ፍትህን በሚያራምድና ከሚገኘው ጥቅም ትልቁን ድርሻ በእርምጃው ለሚነኩ ማህበረሰቦች በሚያስገኝ የስርየት እርምጃ ከደን ምንጣሮና ጉስቁልና ሊከተል ይችል የነበረውን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀት የመቀነሻ ሥርዓት ያዘጋጃል፤
- ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን በየዘርፉና በየክልሉ ለመገንቢያ የሚውል ሃብት የሚያስገኙ ተግባራት ዝግጅትን ያስተባብራል፤ የአቅም ግንባታ ድጋፍንና የምክር አገልግሎትን ይሰጣል፤
- በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ መሠረት ለልማት ፕሮጀክት እና ፕሮግራም የይሁንታ ፈቃድ ከመሰጠቱ በፊት የፕሮጀክቱ እና ፕሮግራሙ ትግበራ በአካባቢ ላይ የሚያስከተለው አሉታዊ ተፅዕኖ በሚመለከተው የዘርፍ ፍቃድ ሰጪ አካል

ወይም በሚመለከተው የክልል አካል ተገምግሞ ውሣኔ የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል፣ ትግበራውንም ያረጋግጣል፤

- ኢትዮጵያ ከተፈጥሮ ሃብቶች መሠረት፣ ከበረሀማነት፣ ከደን፣ ከአደገኛ ኬሚካሎች፣ ከኢንዱስትሪ ቆሻሻዎች እና ከሰው ሰራሽ የአካባቢ አደገኛ ንጥረ ነገሮች ጋር በተያያዘ ያፀደቀቻቸው አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ የአካባቢ ስምምነቶችን በየዘርፉና በየአስተዳደር እርከኑ በመተግበር ወቅት የድግግሞሽ፣ የሃብት ብክነትንና ክፍተትን ለማስቀረት የሚያስችሉ መርሐግብሮችን እና መመሪያዎችን ያዘጋጃል፤ መተግበራቸውንም ይከታተላል፤
- በዓለም አቀፍ የአካባቢ እና የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነቶች ድርድር ላይ ይሳተፋል፣ በዘርፉ አገራዊ ምላሽን በማስተባበሩ በኩል ቁልፍ ሚና ይጫወታል፣ እንደአግባቡ ስምምነቶቹ እንዲፀድቁ ሃሳብ ያቀርባል፤
- ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸውን፣ ዓለም አቀፍ የአካባቢ ውሎች ለመተግበር ተፈላጊ የሆኑ ፖሊሲዎችን፣ ስልቶችን፣ ሕጎችንና መርሐ ግብሮችን እንደሁኔታው ያዘጋጃል፣ ወይም እንዲዘጋጁ ሃሳብ ያመነጫል፣ አዘገጃጀታቸውን ያስተባብራል፤ ሲፈቀዱም በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
- አደገኛ ንጥረ ነገሮችን ወይም ዝቃጮችን ማምረትን፣ ወደ ሀገር ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን፣ እንዲሁም ሕያዋንን በዘረመል ምሕንድስና መለወጥን፣ ልውጥ ወይም ባዕድ ሕያዋንን ወደ አገር ማስገባትን፣ አያያዝንና አጠቃቀምን የሚመለከቱ የአካባቢ ደህንነት ፖሊሲዎችንና ሕጎችን ያዘጋጃል፣ በሥራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፤
- በልማት ዕቅዶችና በኢንቨስትመንት መርሐ ግብሮች ውስጥ የሚካተቱ የአካባቢ የአዋጪነት ማስሊያ ቀመሮችንና የስሌት ሥርዓቶችን ያዘጋጃል ወይም እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤ እንደሁኔታውም በጥቅም ላይ የመዋላቸውን ሂደት ይከታተላል፤
- ዘላቂነት የጎደለው የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ልምድን፣ የአካባቢ ጉስቁልናን ወይም ብክለትን ለመከላከል በሚያስችሉ የመግቻ እርምጃዎች ወይም የማበረታቻ ዘዴዎች መጠቀምን በተመለከተ ሃሣብ ያቀርባል፤
- የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ሥርዓትን ይዘረጋል፤

- የአካባቢና የደን አያያዝን፣ በጥቅም ማዋልንና ፍትሃዊ የጥቅም ተጋሪነትን የሚያራምድ እንዲሁም አረንጓዴ የሥራ ዕድልን የሚፈጥር ምርምርንና የቴክኖሎጂ ሽግግርን ያስተባብራል፣ እንደአስፈላጊነቱ ራሱ ያካሂዳል፤
- አግባብነት ባላቸው የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የአካባቢና የደን ጥበቃ ግዴታዎች መከበራቸውን ለማረጋገጥ በፌዴራሉ ሥልጣን ሥር ወደሚገኝ ማንኛውም መሬት፣ ቅጥር ግቢ ወይም ሌላ ቦታ ይገባል፣ ኃላፊነቱን ለመወጣት ተገቢ ሆኖ ያገኘውን ማንኛውንም ነገር ይፈትሻል፣ ናሙናዎችን ይወስዳል፤
- የሀገሪቱን የአካባቢና የደን እንዲሁም ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚን በሚመለከት ዘገባን በየወቅቱ እያዘጋጀ ያሰራጫል፤
- መደበኛ ያልሆኑ የአካባቢ ትምህርት መርሃ ግብሮችን ያስፋፋል፣ ትምህርቱን ይሰጣል፤ አካባቢያዊ ጉዳዮችን በመደበኛ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ለማካተት አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር ትብብር ያደርጋል፤
- አነስተኛና ሰፋፊ የደን ልማት፣ ቀርከሀን ጨምሮ በግል፣ በወል ይዞታ እና በተፋሰስ ውስጥ እንዲለማና ጥቅም ላይ እንዲዉል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ትግበራውንም ያረጋግጣል፤
- የሀገሪቱ የተፈጥሮ ደን እንዲጠበቅና እንደአስፈላጊነቱ ዘላቂ ጥቅም ላይ እንዲዉል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ትግበራውንም ያረጋግጣል፤
- የተጎዱና የተራቆቱ የደን መሬቶች እንዲያገግሙና የአካባቢያዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸው እንዲሻሻል ሥርዓት ይዘረጋል፣ ትግበራውንም ያረጋግጣል፡፡

## <u>የኮሚሽኑ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል አደረጃጀት</u>

10. የአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚንስትሮች ምክር ቤት ሆኖ በመ/ቤቱ በኃላፊነት የሚመራና የሚያስተዳድር አንድ ኮሚሽነርና ሁለት ምክትል ኮሚሽነሮች ያሉት ሲሆን ኮሚሽኑ በስሩ የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢኒስቲትዩት፣ የአየር ንብረት ለውጥ እና የብዝሃ ሕይወት ዋና ዳይሬክተር፣ የአቅም ግንባታ፣ ትምህርትና ግንዛቤ ዳይሬክቶሬት ጀነራል፣ የፖሊሲ ሕግና ደረጃዎች ጥናት ዝግጅት ዳይሬክቶሬት አሉት፡፡

11. በምክትል ኮሚሽነር ስር ሁለት የሥራ ዘርፎች ያሉት ሲሆን እነሱም የአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ እና የደን ዘርፎች ናቸው፡፡ የደን ዘርፍ ስር 4 ጀነራል ዳይሬክተር ኖሮት በስራቸው 13 ዳይሬክተር፣ የክልልና የፌዴራል አካላት ግንኙነት ኤክስፐርት፣ አለም አቀፍ የደን ንግድና ኢንዱስትሪ ኤክስፐርት፣ የሃብት ግኝትና አለም አቀፍ ግንኙነት ኤክስፐርት፣ የደን ኤክስቴንሽን፣ ትምህርትና የሰው ሃይል ልማት ኤክስፐርትና የክትትልና ግምገማ ኤክስፐርት ያሉት ሲሆን በአካባቢና የአየር ንብረት ለውጥ ዘርፍ 4 ጀነራል ዳይሬክተር ኖሮት በሥራቸው 13 ዳይሬክተር አላቸው፡፡ ከነዚህ የሥራ ክፍሎች ውስጥ የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ክትትል እና ቁጥጥር ጀነራል ዳይሬክተር በቀጥታ ከኦዲት ሥራው ጋር የሚገናኝ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

12. ኮሚሽኑ በመዋቅር የተፈቀደለት 589 ሠራተኛ ቢሆንም በታህሳስ 2011 ዓ.ም በሥራ ላይ ያሉት ሠራተኞች 396 መሆናቸው በተጨማሪም የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ክትትል እና ቁጥጥር ጀነራል ዳይሬክቶሬት በመዋቅር የተፈቀደለት 46 ሠራተኞች ቢሆንም አሁን በሥራ ላይ ያሉት 37 ሠራተኞች መሆናቸው በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የፋይናንስ ምንጭ

13. የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን በአዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣትና በዕቅድ የያዛቸዉን ሥራዎች ለማስፈፀም የሚያስፈልገውን የገቢ ምንጭ የሚያገኘው ከመንግሥት በሚገኝ በጀት ሲሆን በ2008 በጀት ዓመት ብር 50,196,143.68፣ በ2009 በጀት ዓመት ብር 55,563,646.19 እና በ2010 በጀት ዓመት ብር 52,073,894.07 በድምሩ ብር 157,833,683.94 ገቢ ያገኘ ሲሆን በየበጀት ዓመቱ ለተለያዩ ወጪዎች በ2008 ዓ.ም.፣ በ2009 ዓ.ም. እና በ2010 ዓ.ም በቅደም ተከተል ብር 64,636,895.70፣ ብር 89,087,051.07 እና ብር 99,901,030.81 በጠቅላላ ብር 253,624,977.58* ለተለያየ ወጪዎች አውጥቷል፡፡

*የወጪ ሂሳብ የቀረጥ ሂሳብ ክፍያ በገ/ኢ/ል/ት ሚ/ር በኩል የተከፈለን ያካተተ ነው

**<u>በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የአሰራር ሂደት መግለጫ</u>**

14. ከኮሚሽኑ የሥራ ዘርፎች የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ክትትል እና ቁጥጥር ጀነራል ዳይሬክተር ከኦዲቱ ጋር ተያያዥ ሆኖ የተገኘ ሲሆን የጀነራል ዳይሬክቶሬቱ ዋነኛ ተግባራት፡-

- በሃገሪቱ የሚከናወኑ የማምረቻ፣ የአበባ እርሻዎችና ትላልቅ የልማት ፕሮጀክቶች ሲተገበሩ በሀገሪቱ በወጡ ህጎች ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፤
- ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ የልማት ፕሮጀክቶች ሀገሪቱ በተቀበለችውና ባፀደቀችው የዓለም አቀፍ የአካባቢ ስምምነቶችና በሀገሪቱ በወጡ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መፈፀማቸውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፤
- በሃገራችን በሚታየው ፈጣን የከተሞች መስፋፋት፣ በማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ በተሽከርካሪዎችና የህዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት አካባቢ እንዳይበከል የአየር፣ የውሃ፣ የአፈርና የድምጽ ብክለት ያለበትን ደረጃ ለማወቅና ተገቢውን የብክለት መቆጣጠሪያ ስርዓት መዘርጋት የሚያስችሉ ፖሊሲዎች፣ ስልቶችና መርሃ ግብሮች የመቅረጽ፣ የመተግበር፣ ከምርምርና ከከፍተኛ ተቋማት ጋር በቅንጅት የመስራት፣ የማስተባበርና የመምራት ኃላፊነት መወጣት፤
- የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በልማት ሂደት በአካባቢና በሰው ደህንነት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ የአካባቢ ጥበቃ ሥርዓቶችን፤ ደረጃዎችን፤ የአካባቢ መንከባከቢያ መንገዶችንና በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን መቀነሻ ዕቅዶችን ተግባራዊ ለማድረግ፤ ለመቆጣጠር፤ ለመጠበቅ የሚያግዝ አደረጃጀት መፍጠርና መተግበር፤
- የኢንዱስትሪ እና አግሮ ኢንዱስትረ ፓርኮቹ የአካባቢ ሥርዓት እንዲዘጋጅ የሚያስችል የተለያዩ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ጥናታዊ ፅሁፍ ማዘጋጀት፣
- በኢንዱስትሪ እና አግሮ ኢንዱስትረ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ የማምረቻ ተቋማት የምርት ሂደት አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቀባይነት ባለው መንገድ ምርታቸውን እንዲያመርቱ የሚያስችል ሥልጠናና ድጋፍ መስጠት፤
- የኢንዱስትሪ ፓርኮቹ አሰራርና ህግ ተከባሪነትን አስመልክቶ ዘገባ የማዘጋጀት ስራዎች ናቸው፡፡

## <u>የኦዲቱ አላማ</u>

15. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የልማት አጋዥ የሆኑ የማምረቻ ተቋማት የአካባቢ ህጎችንና ደረጃዎችን በማክበር በየትኛውም አካባቢ የሚኖሩ የሀገራችን ዜጐች በጤናና በኑሮ ሁኔታ ላይ ጉዳት ከሚያደርሱ የፋብሪካ ብክለቶች ነጻ እንዲሆኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የሚደጋገፍና የሚናበብ አሰራር መኖሩን፣ ሊለኩ ሊዘገቡና ሊረጋገጡ በሚችሉ መስፈርቶች መሰረት ያደረገ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት መኖሩን በመገምገም የተገኘዉን ጠንካራ ጎን በማበረታታትና ድክመቶችን በመለየት የአምራች ድርጅቶች የአካባቢ ብክለትን ለማስቀረት የሚደረገው የሥራ እንቅስቃሴ ቀጣይነት ያለውና አስተማማኝ ስርዓት በመዘርጋት በተሻለ ብቃት የሚወጣበትን አቅም እንዲፈጥር የማሻሻያ ሀሳብ ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## <u>የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች</u>

16. ከላይ የተመለከተውን የኦዲቱን ዓላማ ለማሳካት በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የኢንዱስትሪ ቆሻሻ/ዝቃጭ/ አወጋገድ ሥርዓት ውጤታማነት በተመለከተ ለተከናወነው የክዋኔ ኦዲት ሦስት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issues/ ተለይተዋል፡፡ እነሱም ፦

    1. በመ/ቤቱ የኢንዱስትሪ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ ፖሊሲዎች፣ አዋጆችና ደንቦች እንዲሁም የማስፈፀሚያ መመሪያዎች፣ ማኑዋሎችና ደረጃዎች መዘጋጀታቸውና ተግባራዊ መደረጋቸው ማጣራት፣
    2. በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ለሚወገዱ የኢንዱስትሪ ዝቃጭ/ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ተገቢው የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት መዘርጋቱን ማጣራት፣
    3. መ/ቤቱ ከኢንዱስትሪ ዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ ጋር በተያያዘ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን፣ እንዲሁም የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋቱን ማረጋገጥ፣

    የሚሉት ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

17. በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡ ሦስት የኦዲት ዋና የትኩረት አቅጣጫዎች 24 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የተመረጡት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና መመዘኛ መስፈርቶች ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ተልከዋል፡፡ የተዘጋጁት የመመዘኛ መስፈርቶች በአባሪ 1 ቀርበዋል ፡፡

## የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

18. ኦዲቱ የተከናወነው በመንግሥት መ/ቤቶች ላይ የክዋኔ ኦዲትን ለማካሄድ ለመሥሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ነው፡፡ ኦዲቱ የሚሸፍነው ከ2008 በጀት ዓመት እስከ 2010 በጀት አመት ድረስ ባለው ጊዜ የተሰራውን ሥራ ሲሆን ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ሆኖ በናሙና በተመረጡ የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች፣ የኢንቨስትመንት ቢሮዎች፣ የንግድ ፍቃድ ሰጪ አካላት፣ ፋብሪካዎች እና ኦዲቱ የሚመለከታቸው የፌዴራል መ/ቤቶች በመሄድ የተለያዩ ከሥራው ጋር አግባብነት ያላቸው መረጃዎችን በመሰብሰብና በመከለስ ለሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብና በአካል በመመልከት ነው፡፡

19. በዚህም መሠረት በናሙና ለተመረጡ በክልል፣ በክልል ከተሞች፣ ዞንና ወረዳዎች ለሚገኙ 12 የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች (ኦሮሚያ፣ አማራ፣ አዲስ አበባ፣ ሞጆ፣ ሰበታ፣ አዳማ፣ ኮምቦልቻ፣ ባህርዳር፣ ደሴ፣ ደቡብ ወሎ ዞን፣ ሎሜና ተሆለደሬ ወረዳዎች)፣ 5 ኢንቨስትመንት ቢሮዎች (የኦሮሚያ፣ የአማራ፣ የሞጆ፣ የኮምቦልቻ ኢንቨስትመንት መ/ቤቶችና የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣)፣ ለ4 ንግድ ፍቃድ ሰጪ አካላት (አማራ፣ የኦሮሚያ፣ የአዲስ አበባ የንግድ ፍቃድ ሰጪ መ/ቤቶች እና ንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር)፣ 2 መሬት አስተዳደሮች (ሞጆ እና ባህርዳር)፣ ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር እና ለ42 ፋብሪካዎች ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ፣ የተለያዩ ማስረጃዎችን በመከለስ እና በአይን ምልከታ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

# የኦዲት ግኝቶች

## ሀ. በመ/ቤቱ የኢንዱስትሪ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ ፖሊሲዎች፣ አዋጆችና ደንቦች እንዲሁም የማስፈፀሚያ መመሪያዎች፣ ማኑዋሎችና ደረጃዎች መዘጋጀታቸውን እና ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ፣

**በኮሚሽኑ የአካባቢ ብክለትን ለመቆጣጠር የወጡ አዋጆች**

***ደንብና መመሪያ መውጣታቱንና ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤***

20. ኮሚሽኑ ከኢንዱስትሪ ዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ ጋር በተያያዘ የወጡ አዋጆችን እና ደንቦችን መሰረት በማድረግ መመሪያ ሊያወጣ እና ተግባራዊ ሊደርጉ ይገባል፡፡

21. በኦዲቱ ወቅት በተከለሱ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች እንዲሁም በቃለ-መጠይቅ በተገኘ መረጃ መሰረት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡-

    - የኢንዱስትሪን ብክለት ለመከላከል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 159/2001 ላይ የተዘረዘሩ ግዴታዎችን ያላከበሩ ፋብሪካዎች ላይ በተጠቀሰው ደንብ አንቀጽ 7 ቁጥር 1 እና 2 እንዲሁም አንቀጽ 12 መሰረት እርምጃ ለመውሰድ (ለምሳሌ ፋብሪካዎችን ፍቃድ ለመሰረዝ፣ ለማገድና ወደ ሌለ ቦታ ለማዘዋወር ወዘተ) መውጣት የሚገባቸው የአፈፃፀም መመሪያዎች አለመውጣታቸው፣
    - የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 ደንብና መመሪያ የሚያስፈለገው ቢሆንም አለመኖሩ ለምሳሌ ጥናቱን ለማዘጋጀት ዘገባውን ለመመርመር የሚረዱ ሃሳቦችን የሚዘረዝሩ መመሪያ፣ ፕሮጀክቱ የሚተገበርበት የህብረተሰብ ክፍል እንዴት መሳተፍ እንዳለባቸው የሚገልፅ ደንብና መመሪያ አለመውጣቱ፤፣

- የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ 300/2001 አንቀጽ 10 ቁጥር 1 እና 2 ላይ ብክለትን ለመከላከል ወይም መጠኑን ለመቀነስ በሚያስችል በማንኛውም ዘዴ መጠቀም ለሚጀምር ለማንኛውም ነባር ድርጅት የሚሰጥ ማበረታቻ በዚህ አዋጅ ሥር በወጣ ደንብ ይወሰናል ቢልም ደንቡ አለመውጣቱ፣፤
- በስራ ላይ የሚገኘውን የአካባቢ ፖሊሲ ሰነድ ከፌደራል እና ከክልል የዘርፍ መ/ቤቶች፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና በአካባቢ ላይ ከሚሰሩ አጋር ድርጅቶች እንዲሁም ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የውጪ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ለመስራት የሚያግዝ የአካባቢ ፖሊሲ ለማዘጋጀት በ2009 ዓ.ም. የታቀደ ቢሆንም አለመዘጋጀቱ፣
- የፋብሪካዎች ክትትልና ቁጥጥርን በተመለከተ የተለያዩ የኢንዱስትሪ ዝቃጭ አያያዝና አወጋገድን መከታተያ ስልቶች ያልተነደፉ/ለመከታተል የሚያስችል የአፈፃፀም መመሪያ አለመውጣቱ (የውሃ ብክለት ክትትል ማድረጊያ /Guideline/……)፣
- እንዲሁም ከፋብሪካዎች የሚወጡ ዝቃጮችን /Sludge/በተመለከተ መልሶ ጥቅም ላይ ለመዋል የተለያዩ ፋብሪካዎች እንደመኖራቸው የየትኛው ዝቃጭ ለየትኛው አገልግሎት መዋል እንዳለበት ለማወቅ የሚያስችል ጋይድላይን የሌለ መሆኑ ፋብሪካዎች መልሶ ለመጠቀም መቸገራቸው፣
- የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 እና የአካባቢ ብክለት ቁጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 ከወጡ የቆዩና  የፋብሪካ ቴክኖሎጂ እያደገ እና የኢንዱስትሪዎች ምርት እየጨመረ እንደመምጣቱ ካለው ተጨባጭ  ሁኔታ ጋር ያለቸው ክፍተቶች ታይቶ አለመሻሻላቸው የአካባቢ ብክለትን ለመቀነስ በሚደረገው ሂደት ላይ ክፍተት መፍጠሩን በናሙና በታዩ ፋብሪካዎችና የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ በተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

22. በሌላ መልኩ የኢንዱስትሪ ዝቃጭ /ቆሻሻ/ አወጋገድን አስመልክቶ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ውስጥ የማይተገበሩ/የሚጣሱ ህጎች ውስጥ የሚከተሉት አሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

- የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 መሰረት በናሙና በታዩ በሁሉም ፍቃድ ሰጪ አካላት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ ባለሀብቶች እንዲያቀርቡ የማይደረግ መሆኑ፣
- የኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 159/2001 መሰረት ድንጋጌውን ለማክበር ፋብሪካዎች በቂ ዝግጅት እንዲያደርጉ የአምስት አመት የእፎይታ ጊዜ የተሰጣቸው ቢሆንም አብዛኛውን ፋብሪካዎች ደንቡን ተግባራዊ ለማድረግ ምንም ተግባር ያልጀመሩ (የአካባቢ አያያዝ እቅድ እና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት የሌላቸው እና አሀድ ያላቋቋሙ፣ የአካባቢ ባለሙያ የሌላቸው፣ በጀት ያልመደቡና የአካባቢ የውስጥ ኦዲት የማያስድረጉ መሆናቸው…) እና ደንቡን ለማክበር የሚያስፈልጋቸውን ስራ ያልጨረሱ ነባር የማምረቻ ተቋማት መኖራቸውን፣
- እንዲሁም ደንቡ በማያከብሩ ፋብሪካዎች ላይ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች እርምጃ እንዲወስዱ ቢደነግግም እርምጃ እየወሰዱ አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

23. ስለጉዳዩ በመ/ቤቱ የሚመለከታቸው ኃላፊ ተጠይቀውና በነባሪዊ ሁኔታ መግለጫ በተሰጠው መልስ ደንብና መመሪያ የሚያስፈልጋቸው ቢኖሩም ሁሉም አዋጆች ደንብና መመሪያ ያስፈልጋቸዋል ማለት እንዳልሆነ ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ አፈጻጸም ላይ የመጡትን ክፍተቶች ለመገምገም የአቅም ውስንነት መኖሩንና የህዝብ ቅሬታዎችን ላይ በማተኮራቸው አዋጆችና መመሪያዎችን ጊዜ ተሰጥቶ ማየት እንዳልተቻለ ሆኖም በአሁኑ ወቅት፡-

    - አዋጅ 299/1995 የወጣው ከ16 ዓመት በፊት በመሆኑ በሥራ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን ለመቅረፍ አዋጁ መሻሻል እንዳለበት ታምኖበት እየተሰራ እንደሚገኝ፣
    - አዋጅ ቁጥር 300/1995 አልተሻሻለም በሚል የተነሳው ግኝት ልክ መሆኑንና በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 10 ላይ ብክለትን ለመከላከል ወይም ለመቀነስ የሚያግዙ ቴክኖሎጂዎችን ነባር ድርጅቶች እንዲስገቡ የሚያስችል የማበረታቻ ደንብ አለመውጣቱን አስመልክቶ ደንቡን ማዘጋጀቱ አስፈላጊ በመሆኑ ባለፈው

አመት ጥናት መደረጉንና ደንቡ ባለመውጣቱም የማበረታቻ ስርዓቱ ተግባራዊ አለመሆኑን፣

- የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 159/2001 አንቀጽ 7 እና 12 ላይ የተዘረዘሩ የፈቃድ ግዴታ ያላከበሩ ፋብሪካዎችን ለማገድና ለመሰረዝ የሚያስችል አፈፃፀም መመሪያ አለመውጣቱን አስመልክቶ እስካሁን ባለው ሁኔታ እንደ ችግር የታየ አለመሆኑንና ለወደፊት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር መመሪያው እንዲዘጋጅ እንደሚያደርጉ፣
- ፋብሪካዎችን ለመከታተል የመከታተያ ስልቶች አለመነደፉንና መመሪያዎችን አለመውጣታቸውን አስመልክቶ በወጡ አዋጆችና ደንቦች ላይ ባሉ መስፈርቶች መሰረት ክትትል እየተደረገ እንደሚገኝና ለወደፊት መመሪያ ጥናትን መሰርት አድርጐ እንደሚዘጋጅ፣
- ከፋብሪካዎች የሚወጡ ዝቃጮች ለምን አገልግሎት እንደሚውል ጋይድላይን አለመውጣቱን አስመልክቶ አስቀድሞ ደረጃ ማውጣት በማስፈለጉ ኮሚሽኑ አለምአቀፍ አማካሪ ቀጥሮ ካለፈው አመት ጀምሮ እየተሰራ እንደሚገኝ፣
- ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የውጪ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ለመስራት የሚያግዝ የአካባቢ ፖሊሲ አስመልክቶ ክለሳ ማስፈለጉ ታምኖበትና ታቅዶ ጥናት በማድረግ ረቂቅ ፖሊሲ የተዘጋጀ እና በየደረጃው ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

24. በተጨማሪም አንድ አንድ የሚወጡ ህጎች ቢዘጋጁም በተለያዩ አካላት ስለሚታዩ ፈጥኖ የመጽደቅና ሥራ ላይ የማዋል ክፍተቶች መኖራቸውን እንዲሁም ትግበራውን በተመለከተ መሰረታዊ የሆነው ችግር ፋብሪካዎች አካባቢን መሰረት ሳያደርጉ የተቋቋሙ፣ ለአጭር ጊዜ ትርፍ ብቻ የሚሰሩ፣ የፋብሪካዎች አቅም አለመኖርና የእፎይታው ጊዜ በራሱ ፋብሪካዎችን ያዘናጋበት ሁኔታ በመኖሩ፣ አንዳንድ ፋብሪካዎች የፈጠሩትን የሥራ እድል እንደማስተማመኛ የመቁጠር /ሠራተኛ ላለማፈናቀል ከመንግስት ጨክኖ እንደማይዘጋባቸው ማሰብ/፣ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶችም በካይ የሆኑ ፋብካዎችን ለመዝጋት የሚፈናቀሉ ሰራተኞችን በማሰብ አስተማሪ በሆነ መልኩ ይሰራ እንደነበር እና ባለድርሻ አካላት ጋር ያለው ትብብርም አነስተኛ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

25. የኮሚሽነሩ የሥራ ኃላፊዎች ይህን ቢሉም ደንብ እና መመሪያ ባለመውጣቱ አዋጁን ተግባራዊ ለማድረግ ባልተቻለበት ሁኔታ “ለሁሉም አዋጆች ደንብና መመሪያ ያስፈልጋቸዋል ማለት አይቻልም…” በማለት ያብራሩት ሃሳብ ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በተጨማሪም የፈቃድ ግዴታ ያላከበሩ ፋብሪካዎችን ለማገድና ለመሰረዝ የሚያስችል አፈፃፀም መመሪያ አለመውጣቱን አስመልክቶ “እስካሁን ባለው ሁኔታ እንደ ችግር የታየ አለመሆኑን” የተገለጸውም በናሙና በታዩ በሁሉም የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ላይ መመሪያው ባለመውጣቱ እርምጃ ለመውሰድ እንደተቸገሩ የገለጹ በመሆኑ ኮሚሽኑ ለወደፊቱ ከአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ጋር ሊወያይበት እና መመሪያው ሊያወጣ እንደሚገባ በመ/ቤታችን ይታመናል፡፡

26. በመሆኑም የአካባቢ ብክለትን መከላከልን አስመልክቶ ሊወጡ የሚገባቸው ደንቦችና የአፈጻጸም መመሪያዎች ያለመውጣታቸው እና የወጡትም አዋጆች ወቅታዊና በየጊዜው የሚለዋወጠውን ቴክኖሎጂን መሰረት ባደረገ ሁኔታ ክለሳ ባለመደረጉ የአካባቢ ባለሙያው እና ባለሀብቱ በኢንዱስትሪ ዝቃጭ/ቆሻሻ/ አወጋገድ በአካባቢ ላይ እያስከተለ ያለውን ተጽእኖ ለመከላከል የአሠራር ክፍተት የፈጠረ መሆኑ፤ እንዲሁም የወጡ አዋጆችና ደንቦችም አገሪቱ ያላትን ተፈጥሮአዊ ሀብቶችን እንደ ወንዝ፣ አፈር የመሳሰሉ በብክለት ምክንያት ተፈጥሮአዊ ምህዳሩ እንዳይጠበቅ በማድረግ ከፍተኛ ጉዳት እያስከተለ ይገኛል፡፡

**በወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ ግንዛቤ**
**ማስጨበጫ መስጠቱንና ለተጠቃሚው ተደራሽ ማድረጉን በተመለከተ፤**

27. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢንዱስትሪ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ በወጡ ፖሊሲዎች፣ ደረጃዎች፣ አዋጆችና ደንቦች ላይ ለአምራች ድርጅቶች ግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጥ እና በተለያየ ጊዜ የሚወጡትን የአምራች ተቋማት /ፋብሪካዎች/ እንዲያውቁ የሚደረግበትን መንገድ ሊያመቻች ይገባል፡፡

28. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት ፋብሪካዎች ውስጥ ቢ.ጂ.አይ ቢራ ፋብሪካ/ኮምባልቻ/፣ አባይ ጣና የምግብ ኮምፕሌክስ/ባህር ዳር/፣ ሴዳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ/ሰበታ/፣ ኤልሲ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ/አዳማ/፣ ሁሃክሱ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ/ኮምቦልቻ/ እና ኮካኮላ ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ /ባህርዳር/፣

ኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ /ኮምቦልቻ/፣ ጂዶንግ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ/በሰታ/ በሚወጡ አዋጆችና ደንቦች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ አግኝተው የማያውቁ መሆናቸው፣

29. እንዲሁም ኮልባ ቆዳ ፋብሪካ/ሞጆ/፣ ኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ /ኮምቦልቻ/ ሀበሻ ቆዳ ፋብሪካ የቆዳ ኢንስቲትዮት እና አይካ/ ጨርቃ ጨርቅ ኢንስቲትዮት /ሰበታ/ ቀጣይ በሆነ መልኩ ያልተሰጣቸው መሆኑ/አንድ ጊዜ ብቻ መሰጠቱ/ ሰራተኛ ሊለቅ የሚችል ከመሆኑ እና የተለያዩ ህጎች በተለያየ ጊዜ እንደመውጣታቸው በተወሰኑ ህጎች ላይ ብቻ ግንዛቤ ያላቸው መሆኑ፣

30. በተጨማሪም በየጊዜው የሚወጡ የአካባቢ ብክለትን የተመለከቱ አዳዲስ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን ተደራሽ የሚደረግበት ሥርዓት አለመኖሩ ማለትም በመ/ቤቱ ድረ-ገጽ ላይ ያልተጫኑ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከፋብሪካዎቹ በቃለ መጠይቅ በተገኘ መረጃ እና ከኮሚሽኑ ድረ-ገጽ ለማወቅ ተችሏል፡፡

31. ጉዳዩን አስመልክቶ የኮሚሽኑ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ አለም አቀፍ የሆኑ ፋብሪካዎች ህጎቹን እንደሚያውቋቸው ባለሙያዎች ሲቀየሩና በሌላ ባለሙያ ሲተኩ በድጋሚ የመስጠት ክፍተት ሊኖር እንደሚችልና ከፋብሪካ ብዛት አንጻር እንደፌዴራል መ/ቤት ሁሉም ጋር መድረስ እንደሚከብድና ክልሎችም በጀት መድበው እንዲሰጡ ለማድረግ ያለው በጀት በቂ ነው የሚለው መታየት እንዳለበት እና በነሱ በኩል በካይ የሆኑት ቆዳና ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች ትኩረታቸውን እንደወሰዱባቸው እና ፋብሪካዎች የአካባቢ ባለሙያ እንዲቀጥሩ አሃድ እንዲያቋቁሙ የሚጠበቅ ሲሆን የአካባቢ ባለሙያ ቢኖራቸው ግንዛቤው ስለሚኖረው ክፍተቱ ሊቃለል እንደሚችል ገልጸው በየጊዜ የሚወጡ ህጎች የበፊቶቹም በድረ-ገጽ ላይ መጫናቸውንና አዲስ የሚወጡት ላይ ከአይቲ ክፍል ጋር እንደሚነጋገሩበት ገልጸዋል፡፡

32. በተጨሪም ጉዳዩን አስመልክቶ በኮሚሽኑ በነባሪዊ ሁኔታ መግለጫ በቀረበው ምላሽ ላይ በደንብ ቁጥር 159/2001 መሰረት የደንቡን ድንጋጌዎች ሙሉ ለሙሉ በአምስት አመት ውስጥ ፋብሪካዎች ተግባራዊ እንዲያደርጉ የተለያዩ ግንዛቤ ማስበጫ ሲሰጥ መቆየቱን ሆኖም የሰው ኃይል መቀያየር አንጻር ሲታይ የተሰጠው

ግንዛቤ በቂ ነው ተብሎ እንደማይታመን እና ተከታታይነት ያለው ግንዛቤ ሥራ ለመስራት ጥረት እንደሚደረግ ተገልጿል፡፡

33. ሆኖም የመ/ቤቱን ድረ-ገጽ በተመለከተ የተጫነ አዋጅም ሆነ መመሪያዎች አለመኖራቸውን ከመ/ቤቱ ድረ-ገጽ ያረጋገጥን ሲሆን ከላይ በሪፖርት ቁጥር 28 እንደተገለጸው ምንም አይነት ግንዛቤ ማስጨበጫ ያላገኙ የማምረቻ ተቋማት መኖራቸው በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

34. በመሆኑም ሥራው ከክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ጋር በመነጋገር ቢያንስ ግንዛቤውን የሌላቸውንና የሚያስፈልጋቸውን ፋብሪካዎች በመለየት ግንዛቤውን አለመሰጠቱ የሚወጡ ህጎችን እንዳይተገበሩ ተጠቃሽ ከሚሆኑ ምክንያቶች አንዱ ሆኗል፡፡

**በኮሚሽኑ ለኢንዱስትሪ ዝቃጭ/ቆሻሻ/**

**<u>የሚያገለግሉ ደረጃዎች መውጣታቸውን በተመለከተ</u>፤**

35. ኮሚሽኑ አግባባ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመመካከር ለኢንዱስትሪ የቆሻሻ ዓይነቶች አመነጫጨት፣ አያያዝ፣ አከመቻቸት፣ አመካከን፣ አጓጓዝ እና አወጋገድ የሚያገለግሉ የመጠን እና የአተገባበር ደረጃዎችን ሊያወጣ ይገባል፡፡

36. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎ እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታየው የኢንዱስትሪ ዝቃጭ አመነጫጨት፣ አያያዝ፣ አከመቻቸት፣ አመካከን፣ አጓጓዝና አወጋገድ የሚያገለግሉ የመጠን እና የአተገባበር ደረጃዎች አለመውጣታቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡

37. በናሙና ከታዩት የተለያዩ አምራች ድርጅቶች የሥራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ ከፍሳሽ ቆሻሻ ማከሚያ (Sedimentation tank) የሚወጣ የፍሳሽ ቅሪት (Sludge Cake) ደረጃውን የጠበቀ ስለመሆኑ እርግጠኛ ሳይሆኑ እና የሚያስከትሉት ጉዳት ሳያረጋግጡ በተለያየ መንገድ እያስወገዱ ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ፡-

- በግቢያቸው ውስጥ የሚያቃጥሉ ጸሐይ ቀለም ፋብሪካ፣
- ለተለያየ ጥቅም የሚያውሉ አይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ለቦሎኬት መስሪያ፣

- ቢ.ጂ.አይ ቢራ ፋብሪካ ለግቢ ውስጥ ለአትክልት በማዳበሪያነት፣
- ወደ ወንዝ በመድፋት ሆዶቼ፣ ሆራ፣ ዚንግዛንግ፣ ሞጆና ኮልባ ቆዳ ፋብሪካዎች፣
- በግቢ ውስጥ ጉድጓድ ቆፍረው በመቅበር ዲ.ኤክስ ቆዳ ፋብሪካ እና ኮካ ኮላ ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ፣

38. እንዲሁም በናሙና ከታዩት በባህርዳር ከተማ ሀበሻ እና በባህርዳር ቆዳ ፋብሪካዎች፣ በሞጆ ከተማ ኢስት አፋሪካ፣ ፍሬንድ ሺፕ፣ ጆርጅ ሹ ቆዳ ፋብሪካዎች በከተሞቹ (ሞጆና ባህርዳር) መርዛማ ለሆኑ ቆሻሻዎች የተለየ ቦታ የሌለና የደረቅ ቆሻሻ የሚጥሉበት ቦታ አጥር የሌለውና ደረጃውን ያልጠበቀ ቢሆንም ምንም አይነት ማጣራት ሳይደረግለት (ሳይታከም) ወደ ከተሞቹ የደረቅ ቆሻሻ መጣያ የሚጥሉ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ከሥር በምስል 1 ላይ እንደሚታየው በባህርዳርእነዚህ ኬሚካልነት ያላቸው ቆሻሻዎች በሚጣልበት ቦታ በቆሻሻነት የተጣሉ እቃዎችን ከቆሻሻ ቦታው ላይ ተገኝተው የሚለቅሙ ሰዎች መኖራቸውን የኦዲት ቡድኑ በቦታው ላይ በመገኘት ለመመልከት ችሏል፡፡

39. በተጨማሪም በሰበታ ከተማ በአሁኑ ወቅት አንዳንድ ፋብሪካዎች ወደ ከተማዋ ቆሻሻ መድፊያ እንዳይጥሉ እና በግቢያቸው ውስጥ እንዲይዙ የተደረገ ቢሆንም የተፈቀደው ቆሻሻ መድፊያ በአጥር ያልተከለለ፣ በወንዝ ዳር ያለ እና በቀላሉ በጎርፍ እየታጠበና እየተገፋ ወደ ወንዙ በመግባት ለወንዙ ብክለት የራሱ ድርሻ መኖሩን ለአካባቢ ጥበቃ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

40. በተመሳሳይ በአዲስ አበባ ከተለያዩ ፋብሪካዎች የሚወጣው ዝቃጮች/ቆሻሻ ምንም አይነት የማጣራት ሂደት/ሥራ/ ሳይደረግለት የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ላይ ማለትም በቆሼ/በረጲ እያስወግዱ መሆኑ፤ እንዲሁም የተጠቀሰው ቦታ ደረጃውን የጠበቀ ባለመሆኑ የደረቅ ቆሻሻ ደረጃ እስከሚወጣለት ፋብሪካዎቹ በግቢያቸው እንዲይዙ በታህሳስ 2010 ለከተማ መስተዳደሩ በተጻፈ ደብዳቤ ያሳወቀ ቢሆንም ድርጊቱ ስለመቆሙ ክትትል ስለመደረጉ ማስረጃው አልቀረበም፡፡

ምስል 1 የባህርዳር ከተማ  ቆሻሻ መጣያ



41. ጉዳዩን አስመልክቶ ለሚመለከታቸው የሞጃ ከተማ የመሬት አስተደርና የአማራ ክልል አካባቢ ጥበቃ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ የባህርዳር ከተማ ቆሻሻ መጣያ ለወደፊት አሁን ባለበት ቦታ ዘመናዊ በሆነ መልኩ የማከም ሥራ ለማሰራት መንግሥት ከአለም ባንክ የተገኘ ገንዘብ መመደቡን እና በሞጆ ከተማ የከተማዋ ኘላን ሲሰራ የጠጣር ቆሻሻ ማስወገጃ ባለመኖሩ ጊዜያዊ መድፊያ ወንዝ ዳር ያለና በዝናብ ታጥቦ ወደ ወንዝ እንዲገባ ታሳቢ ተደርጎ የተዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

42. ስለጉዳዩ በመ/ቤቱ የሚመለከታቸው ኃላፊ ተጠይቀውና በነባሪዊ ሁኔታ መግለጫ በተሰጠው መልስ በመ/ቤቱ ከ700 በላይ ደረጃዎች መውጣቸውን ነገር ግን የአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ደረጃዎቹን ለመስራት የቴክኖሎጂና የሰው ኃይል አቅም አለመኖሩን አስረድተው የዝቃጭ ደረጃዎቹን ለማውጣት ኘሮፖዛል በማዘጋጀት ለደረጃዎች ኤጀንሲ የተላከ መሆኑንና የደረጃዎች ኤጀንሲም ለዝግጅቱ የባለሙያዎች ቡድን አቋቁሞ እየሰራ እንደሚገኝ፣ የቆሻሻ አያያዝ ላይ ተቋማቱ የሚያመነጩት ቆሻሻ ማስወገጃ ደረጃውን የጠበቀ ቦታ አለመኖሩን አስመልክቶ

በኮሚሽኑ እርምጃ እንዲወሰድ ግብረ መልስ የተሰጠ ቢሆንም የከተማ መስተዳደሮቹ የቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ የሌላቸው በመሆኑ ተጨማሪ ችግር መፍጠሩን ገልጸዋል፡፡

43. የኮሚሽኑ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የችግሩን አሳሳቢነት ተረድተው ችግሩን ለመቅረፍ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት የሰሩት ሥራ ባለመኖሩ ኃላፊነታቸውን እንዳልተወጡ ያሳያል፡፡

44. በተጨማሪም አብዛኞቹ ቆዳ ፋብሪካዎች ቆዳ በ(Chromium Sulphate) ከለፋ በኋላ የሚወጣ የዌት ብሉ ቁርጥራጮች እና ሌሎች ደረቅ ቆሻሻዎች ከሰው ንክኪ ባልጸዳ መልኩ በግቢ ውስጥ እና ከግቢ ውጭ የሚጥሉ ቆዳ ፋብሪካዎች (ኢትዮ፣ ኮምቦልቻ፣ ኮልባ፣ ኢስት አፍሪካ፣ ፍሬንድሺፕ፣ ሆዶቹ፣ ሆራ፣ ሞጆ፣ ዚንግዛንግ፣ አዲስ አበባ፣ ድሬ፣ ባቱ ቆዳ ፋብሪካዎች)መኖራቸውን ከመስክ ምልከታና ከተከለሱ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፣

45. በመሆኑ ደረጃቸውን ያልጠበቁ የኢንዱስትሪ ዝቃጮች በሰውና በእንስሳ ጤና እንዲሁም በአካባቢ ላይ ሊያደረሱ ከሚችሉት ጉዳት አንጻር ደረጃዎቹ ትኩረት ተሰጥቷቸው አለመውጣቸው አግባብ አይደለም፡፡

**ምስል 2 ኢትዮ ቆዳ ከፋብሪካው ጀርባ የሚጣሉ የፋብሪካው የሚወጣ ዌት ብሉ ቁርጥራጭ**



መኖሪያ ቤቶች

ምስል 3 ኮልባ ቆዳ ፋብሪካ ከፋብሪካው ግቢ ውጭ የሚወገድ ቆሻሻ

ምስል 4 ኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ /ሐይቅ/ በግቢ ውስጥ የሚጣሉ የቆዳ ልፋጮች

**ወደ ውሃ አካላት እና ወደ ፍሳሽ መቀበያ መስመሮች**

**<u>የሚለቀቁ ፍሳሾችን ደረጃ መውጣቱን በተመለከተ</u>፤**

46. ኮሚሽኑ ወደ ውሃ አካላትና ወደ ፍሳሽ መቀበያ መስመሮች የሚለቀቁ ፍሳሾች ደረጃዎችን ሊያወጣ ይገባል፡፡

47. በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች በታየው መሰረት ከፋብሪካዎች የሚወጡ ፍሳሾች ደረጃቸውን እንዲጠብቁ የፍሳሽ ማከምያ መሳሪያዎች ደረጃ እንደሚከተለው ተብራርቷል፡-

- መለስተኛ የመጀመሪያ ደረጃ ማከምያ መሳሪያዎች ማለት በፍሳሽ ቆሻሻዎቹ ውስጥ ያለውን በአንጻራዊ መልኩ ግዙፍ ጠጣር ነገሮችን እና ፍሳሹን ለመለያት ብቻ የሚገለግል መሳሪያ ነው፡፡ በመሆኑም በተናጠል የዚህ መሳሪያ በአንድ የቆዳ ፋብሪካ መኖር በአካባቢ ደረጃ የተቀመጡትን ከቆዳ ማምረቻ ተቋማት የሚለቀቁት በካይ ነገሮች ፓራሜትሮች ለማከም የማያስችል መሆኑ፣
- የመጀመሪያ ደረጃ (ፊዚካላዊና ኬሚካላዊ) ማከምያ መሳሪያ ማለት የሚዘቅጡ የካርቦን ውሁዶችና ካርቦን አልባ ውሁዶች በማጥለል በካዮቹን የሚለይ መሳሪያ ሲሆን፣ በአካባቢ ደረጃው የተቀመጡት ፓራሜትሮች 25-50 በመቶ ባዮሎጂካል ኦክሲጅን ዲማንድ፣ 50-70 በመቶ ተንሳፋፊ ጠጣር ነገሮች እንዲሁም 65 በመቶ ዘይትና ሌሎች ቅባት ነክ በማከም የሚያስወግድ መሆኑ፣ (ፓራሜትሮቹ በአባሪ ሁለት ተያይዟል)

- ሁለተኛ ደረጃ (ስነ ህይወታዊ) ማከምያ መሳሪያ ማለት ከመጀመሪያ ደረጃው ጋር በቅብብሎሽ የሚሰራ ማከምያ መሳሪያ ነው፡፡ የመሳሪያው ዋና ተግባር ስነ-ህይወታዊ በሆነ መንገድ በፍሳሽ ቆሻሻው ውስጥ ከሚገኙ ደቂቅ ፍጥረታት ጋር ተብላልተው ሊወገዱ የሚችሉትን ንጥረ ነገሮችን የሚያስወግድ መሆኑ፣
- የክሮምየም ንጥረ ነገር ማለት ዳግም ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል መሳሪያ ሲሆን፣ ይህ መሣሪያ ከቆዳ ፋብሪካዎች የሚለቀቀውን ክሮምየም የተባለ መርዛማ ንጥረ ነገር ከሌሎች ውጋጆች በመለየት፣ ንጥረ ነገሩ ዳግም ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግ ንጥረ ነገሩ በአካባቢና በሰዎች ጤና ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችል መሳሪያ ነው፡፡

48. ይሁን እንጂ ከፋብሪካዎች የሚወጡ ወደ ውሃ አካላትና ወደ ፍሳሽ መቀበያ መስመሮች የሚለቀቁ ፍሳሾችን በተመለከተ አገር አቀፍ ደረጃ ያለ ሲሆን በኦዲቱ ወቅት በናሙና ተመርጠው ከታዩት ፋብሪካዎች በተደረገው ማጣራት አብዛኞቹ ደረጃውን ያልጠበቀ/የተበከለ ውሃ/ ወደ ፍሳሽ መቀበያ እና ወደ ወንዞች የሚለቁ መሆናቸውን የኦዲት ቡድኑ በፋብሪካዎቹ በመገኘትና በአካል በማየት፣ በናሙና ለተመረጡ የአካባቢ ጥበቃ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ-መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል። ዝርዝር ጉዳዩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡
   - በሞጆ ከተማ 17 የቆዳ ፋብሪካዎች ያሉ ሲሆን በናሙና ከታዩት 14 ቆዳ ፋብሪካዎች ውስጥ 10 ፋብሪካዎች ውስጥ የመጀመሪያ ደረጃ የፍሳሽ ማከምያ መሳሪያዎች ብቻ ያላቸው ሲሆን በተቀሩት አራቱ (ዲኤክስ፣ ፈሪዳ፣ ጆርጅ ሹ፣ ዩናይትድ ኘዚን) ቆዳ ፋብሪካዎች 2ኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ ያላቸው ቢሆንም 3ኛ የፍሳሽ ማከሚያ ባለመኖራቸው ምክንያት የብክለት መጠናቸው ቢለያይም ሁሉም ደረጃውን ያልጠበቀ ፍሳሽ ወደ ሞጆ ወንዝ የሚለቁ በመሆናቸው በወንዙ ላይ ከፍተኛ ብክለት እያደረሱ የሚገኙ መሆኑ፣
   - በሰበታ ከተማ በናሙና ከታዩት 7 ፋብሪካዎች አራቱ (ባለዛፍ እና ብሔራዊ አረቄ ፋብሪካ፣ ጂዶንግ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ አይካ አዲስ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ) ወደ ሀጠበላ ወንዝ እና ወደ ፍሳሽ መስመር የተበከለ ውሃ የሚለቁ መሆናቸው፣ በተጨማሪም በአሁኑ ወቅት ሴዳ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ በብልሽት ምክንያት፣ ሀፋዳ እና ብሉ ናይል ቆዳ ፋብሪካዎች በአካባቢ ብክለት

ምክንያት እስከ ብሉ ኘሪንት ያለው ምርት እንዲቆም (ካቆሙ ዘጠኝ ወር ሆኗቸዋል) የተደረገ ቢሆንም ላለፉት አመታት ወደ ሀጠበላ ወንዝ ደረጃውን ያልጠበቀ ፍሳሽ በመልቀቅ ሲበክሉ መቆየታቸው፣

- በአዲስ አበባ ከ7 ቆዳ ፋብሪካዎች ውስጥ ስድስቱ የቆዳ ፋብሪካዎች 1ኛ ደረጃ የፍሳሽ ማከሚያ ብቻ ያላቸው በመሆኑና ይርጋለም ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ የፍሳሽ ማጣሪያ ባለመኖሩ ምክንያት የአለም አቀፍ ደረጃውን ያልጠበቀ(ከ6 እስከ 9 ያሉ ፓራሜትሮች ላይ ከተፈቀደው የልቀት ደረጃ በላይ) ላይኛውና ታችኛው የአቃቂ ገባር ወንዞች የሚለቁ ሲሆን በተጨማሪም በአዲስ አበባ 90 በመቶ የሚሆኑ ፋብሪካዎች አቃቂ ክፍለ ከተማ ከትንሹ አቃቂ ወንዝ 50 ሜትር አካባቢ የሚገኙ በመሆናቸው አቃቂ ወንዝ በከፍተኛ ሁኔታ እየበከሉ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በአዲስ አበባ ያሉ ትልልቅ ፋብሪካዎች ሞሃ ለስላሳ ፋብሪካ፣ ብሔራዊ አልኮል ፋብሪካ፣ አዋሽ ወይን ጠጅ አክሲዮን ማህበር፣ ብሔራዊ ትምባሆ ድርጅትም ያለምንም የፍሳሽ ማጣሪያ ከተፈቀደው የልቀት ደረጃ በላይ የሚለቁ መሆናቸው፣
- በኮምቦልቻ ከተማ ሁሃክሱ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ እና በቱሁለዶሬ ወረዳ ኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ (ሐይቅ) 1ኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ ብቻ ያላቸው በመሆኑ፣ ኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሦስት ሼዶች ላይ ሙሉ ለሙሉ ሥራ የጀመረ ቢሆንም የተገነባው ማጣሪያ ሥራውን ባለመጀመሩ እና ደሴ ቁራ ፋብሪካ የፍሳሽ ማጣሪያ ቴክኖሎጂ ባለመኖሩ፣ ኢትዮ ቆዳ ፋብሪካ በሎሜ ወረዳ (ኤጀርሳ) ሁለተኛ ደረጃ ቢኖረውም ሦስተኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ የሌለው በመሆኑና ሁሉም ደረጃውን ያልጠበቀ/ያልተጣራ ፍሳሽ አብዛኞቹ ወደ ቦርከና፣ ኢዮሌ እና የመሳሰሉት ወንዞች የሚለቁ በመሆናቸው በወንዛቹ ላይ ብክለት እያደረሱ መሆኑ፣ በተጨማሪም ኢትዮ ቆዳ ፋብሪካ የፍሳሽ ማከሚያ ቢኖረውም ከስር በምስል 5 ላይ እንደሚታየው ከፍተኛ መጠን ያለው ያልታከመ ፍሳሽ በትነት የሚያስወግድ ሲሆን ፍሳሹ ወደ ሥር በመስረግ በአፈር ላይ እና በሚተንበት ወቅት በአየር ላይ ብክለት ሊያደርስ የሚችል ከመሆኑም በላይ ፍሳሹ ከመሙላቱ የተነሳ ዝናብ ቢዘንብ ወይም ተጨማሪ ፍሳሽ ቢገባበት ወደ ውጭ ሊፈስ የሚችል መሆኑ፣

- በተመሳሳይ ባህርዳር ከተማ ጸሐይ ቀለም ፋብሪካ ያልታከመ ውሃ በትነት የሚያስወግድ ሲሆን አማራ ፓይኘ የፍሳሽ ማጣሪያ ባለመኖሩ፣ ሀበሻ ቆዳ ፋብሪካ የመጀመሪያ ደረጃ ብቻ በመኖሩ እና ባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ የመጀመሪያው የፍሳሽ ቆሻሻው Collection Tanker ፍሰት ከተቀመጠው የማጣራት ሳይክል ስርዓት ውጭ በOver Flow በማድረግ በቀጥታ ያልተጣራ ውሃ ወደ ጣና ሀይቅ እና አባይ ወንዝ የሚለቁ መሆናቸው እንዲሁም ኮካኮላ ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መሳሪያዉ የሚሰራ ቢሆንም ከማጣሪያ መሳሪያው በቀጥታ ወደ ማስወገጃ ቱቦ በማያያዝ አልፎ አልፎ በሚለቀቅ ያልተጣራ ፍሳሽ ቆሻሻ ወደ ውጭ በመልቀቅ ብክለት እያደረሱ መሆናቸውን ለፋብሪካዎቹ የሥራ ኃላፊዎች ከቀረበው ቃለ መጠይቅ፣ ከአባባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በተገኙ እና በተከለሱ ማስረጃዎችና የኦዲት ቡድኑ በአካል በመገኘት ባደረገው ምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**ምስል 5 ኢትዮ ቆዳ ፋብሪካ ሁለተኛ ደረጃ የፍሳሽ ማጣሪያ ቢኖረውም መጠኑ ብዙ የሆነ ፍሳሽ በትነት እያስወገደ ይገኛል**



**ምስል 6 አገልግሎት ያልጀመረው የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ የፍሳሽ ማጣሪያ**



49. በተጨማሪም ከጥቂት ፋብሪካዎች /ኢትዮ ቆዳ፣ ቢጂአይ ቢራ ፋብሪካ፣ ኮካ ኮላ ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ/ በስተቀር በተቀሩት ፋብሪካዎች ቤተ-ሙከራ የሌላቸው እና ወደ ወንዝ ወይም ወደ ፍሳሽ መስመር የሚለቀቁ ውሃዎች ደረጃውን የጠበቀ ስለመሆኑ ቀጣይነት ባለው መልኩ በቤተ-ሙከራ የማይስመረምሩ መሆናቸው በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ ትክክለኛ ደረጃውን የሚያሳይ ሰንጠረዥ በአባሪ ሁለት ተያይዟል፡፡

50. ከላይ የታዩት አብዛኛው ወንዞች የአዋሽ ገባር ወንዞች ሲሆኑ በ2009 ዓ.ም. ከአፋር፣ ከአማራና፣ ከኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት እንዲሁም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ በአስር ዋና ዋና የአዋሽ ገባር ወንዞች ላይ ማለትም ቦርከና፣ ሚሌ፣ ከሰም፣ ሞጆ፣ ወሬርሶ፣ አቃቂ፣ ቀበና፣ ሎሜ፣ ሀጠበላና ጊንጪ በኮሚሽኑ በተደረገ የብክለት ክትትል ሪፖርት ሀጠበላ (Dissolved Oxygen 2.8 ሚሊ ግራም/ሊትር፣ Total Dissolves solids=1300 ሚሊ ግራም/ሊትር) ከሚጠበቀው ደረጃ በታች መሆናቸዉ አንድ ተፈጥሮአዊ ወንዝ ህይወትን ማኖር የሚያስችል የሚሟ የኦክስጅን መጠን በአማካኝ ቢያንስ ከ6.00 ሚሊ ግራም/ሊትር ማነስ እንደሌለበት Guideline for Surface water quality standard ላይ የተገለጸ እና ዉሃዉ የአካባቢዉን ማህበረሰብ የእንስሳት ሀብት ልማት ስራ እየጎዳ መሆኑን፣

51. ቀበና (DO=3.5ሚሊግ/ሊ፣ Total Dissolves solids S=375ሚሊግ/ሊ)፤ አቃቂ (DO=3.9 mg/lit፣ TDS=518 mg/lit)ና ሞጆ(DO=2.5ሚሊግ/ሊ፣ TDS=317ሚሊግ/ሊ)

ሲሆን እነዚህና መሰል መስፈርቶች በሶስቱ ወንዞች ውስጥ እንደ ዓሳ ላሉ ዉሃ ውስጥ ለሚኖሩ እንስሳት/Aquatic animals/ ለመኖር ሊያዳግታቸው እንደሚችል፣ በተጨማሪ ከወንዞች የተወሰዱት የውሃ ናሙናዎች ለቤተ ሙከራ ፍተሻ የሞጆ ወንዝ የከባድ ብረት አሰተኔ/Heavy metals/ ይዘት ካድሚየም (0.034ሚሊግ/ሊ)፣ ክሮሚየም (0.33 ሚሊግ/ሊ)፣ እርሳስ(Lead)[0.26ሚሊግ/ሊ) እንዲሁም የአቃቂ ወንዝ ከባድ ብረት አስተኔ(Heavy metals) ካድሚየም(0.04 mg/lit)፣ ክሮሚየም (0.52ሚሊግ/ሊ)፣ እርሳስ(Lead)[0.3ሚሊግ/ሊ) ከደረጃው በላይ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ እንዲሁም በ2010 በአስሩም ወንዞች ላይ በቤተ-ሙከራ ተመርምሮ ማንጋኒዝ 0.3 ሚሊግ/ሊ፣ ሰልፌት 200ሚሊግ/ሊ እና ክሎራይድ 250 ሚሊግ/ሊ በሁሉም ወንዞች ላይ ከደረጃ በላይ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በተጨማሪም ወንዞቹ የአካባቢውን ማህበረሰብ ሊበክል የሚችል ከፍተኛ ሽታ እንዳላቸው የኦዲት ቡድኑ በቦርከናና በሞጆ ወንዝ በአካል በመገኘት ለመረዳት ተችሏል፡፡

ሞጆ ወንዝ በአካባቢው በፋብሪካዎች በሚደርስበት ብክለት ቀለሙ መቀየሩን የሚያሳይ ምስል 7





52. በአጠቃላይ በአዋሽ ተፋሰስ ውስጥ 9 ቢራ ፋብሪካ፣ 8 የኬሚካልና የኮንስትራክሽን ግብዓት ፋብሪካ፣ 12 የምግብና የለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ፣ 34 የቆዳና የቆዳ ውጤቶች ፋብሪካ፣ 55 የጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ 13 የወተትና የስጋ ፋብሪካ፣ 115 የብረታ ብረት ፋብሪካ በጠቅላላው 246 ፋብሪካዎች በመኖራቸው እና በኢንዱስትሪዎቹ የተለያየ ይዘት ያለው ቆሻሻ (Colloidal and Dissolved Organic Substances, High Toc, Toxic Benzen Derivatives, High BOD, High Suspended Solids Colloidal and Dissolved Organic Substances, Odors, Total Solids, Hardness, Chlorides, sulphides, Chromium, Alkaline Effluent, Suspended Solids, Nitrogen, High fecal Coliforms and streptococci, High Content of toxic/Heavy metals)በቅደም ተከተል የሚያመነጩ መሆናቸውን ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

53. በተጨማሪም በኮሚሽኑ በተገኘና በተከለሰ መረጃ ከማምረቻ ተቋማቱ የሚመነጩ ከላይ የተገለጹት አደገኛ ንጥረ ነገሮች በውሃ አካላት ተበራክቶ መገኘት ወይም በአካባቢ ደረጃዎች ከተቀመጠው መስፈርት በላይ መሆናቸው እና የተበከለ ውሃ በምንጭነት በሚጠቀሙ ማሳዎች ላይ የሚበቅሉ የምግብ አይነቶች መመገብ ለተለያዩ በሽታዎች ሊያጋልጡ እንደሚችሉ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፤ ንጥረ ነገሮቹ የሚያደርሱት ጉዳትን በተመለከተ፤

- ክቡድ ብረታ ብረቶች (Heavy Metals) lead፣ arsenic፣ cadmium፣ cobalt፣ chromium፣ copper እና silver ሲሆኑ ከፊሎቹ በአነስተኛ መጠን ለሰውነታችን በጣም አስፈላጊ ቢሆኑም በሰውነታችን ውስጥ ያለው የክቡድ ብረታብረቶች መጠን ከፍ ባለ ቁጥር አዝጋሚ ወይም ቅጽበታዊ መመረዝን እንደሚያስከትል ባጠቃላይ ክቡድ ብረታ ብረቶች በትንፋሽ፣ በመብል እና በቆዳ ንኪኪ አመካኝነት በሰዎች ሰውነት ውስጥ በመግባት በተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ማለትም በሳንባ፣ የሴላችን ስብ፣ አጥንት፣ ዕጢ እና ጸጉር ውስጥ እንደሚከማቹ ለክቡድ ብረታብረቶች በመጋለጥ የሚከሰተው መመረዝ የነርቭ ስርዓት በአግባቡ እንዳያከናውን የሚያደርግና ከዚህ ባሻገር በኩላሊት፣ በሳንባ እና በጉበት ላይ ጉዳት ሊያስከትል እንደሚችል እና በተደጋጋሚ ለክቡድ ብረታብረቶች መጋለጥ ለካንሰር በሽታ እንደሚዳርግ፣
- BOD5mg/L ባዮኬሚካል ኦክስጂን ዲማንድ እና COD/mg/l ኬሚካል ኦክስጂን ዲማን በውሃው አካላቱ ውስጥ የሚገኘውን የሟሟ የኦክስጅን መጠን የሚቀንስ በመሆኑ በውሃ አካላቱ ውስጥ የሚገኙት ደቂቅ ፍጥረታት እና ህልውናቸው በነሱ ላይ የሆኑት ሌሎች ህያው የሆኑት ነገሮች እንደሚጠፉ፣
- የናትሮጅን እስስር (bond) (Total Nitrogen and Total ammonia) በአካባቢ ከመጠን በላይ መገኘት ከብቶች ከሚያስፈልጋቸው በላይ በናይትሮጅን የበለጸጉ ምግቦች በሚመገቡበት ወቅት ለጤና ጉዳት የሚዳርግና ወቅቱ ያልጠበቀ የእጽዋት እድገት እና የውሃ አቅላሚ መበራከት እንዲሁም በውሃ ውስጥ ብስባሽ በማበራከት በውሃው ውስጥ ያለው የኦክስጅን ፍላጎት ወይም የኦክስጅን መጠን እንዲቀንስ ማድረጉ፣
- ክሎራይድ በዋናነት በቆዳ ፋብሪካዎች ጥቅም ላይ የሚውል ንጥረ ነገር ሲሆን የቆዳ ፋብሪካዎች በተለያዩ የምርት ሂደት ውስጥ ጨው ጥቅም ላይ ስለሚያውሉ ከማምረቻ ተቋማት የሚለቀቀው ፍሳሽ ጨዋማ መሆን በውሃ ውስጥ ባሉት አካላት ላይ ጉዳት ከማድረሱም በተጨማሪ በአፈር ውስጥ ጨው እንዲከማች በማድረግ የእርሻ ቦታዎች ጨዋማ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ይህ ሁኔታ የተክሎች እና እጽዋቶች የውሃ ስርገት እንዲቀንስ በማድረግ ምርትና ምርታማነት እንደሚቀንስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

54. በናሙና በታዩ በሞጆ፣ በአዲስ አበባ፣ በኮምቦልቻ፣ በሰበታና በባህርዳር የአካባቢ ጥበቃ ኃላፊዎች በተገኘ መረጃ እነዚህ ወንዞች የአካባቢ ማህበረሰብ ለተለያዩ አገልግሎቶች(ለመስኖ፣ ልብስ እና ገላ ለመታጠብ ለከብቶች የመጠጥ ውሃ) የሚያውላቸው ሲሆን ከብቶች የሚጠጡት በመሆኑ የመክሳት፣ ቆዳ የመላጥና ወተት የመከልከል በስተመጨረሻም እስከ ሞት የሚደርሱ መሆናቸውን ከማህበረሰቡ በሚመጡ ቅሬታዎች እና ችግሩ ወደ ተከሰተበት አካባቢ በመሄድ ለማየት እንደቻሉ፤ በተጨማሪም በመስኖ ለጓሮ አትክልትነት የሚጠቀሙ በመሆናቸውም በአሁኑ ወቅት በሀገራችን እየጨመሩ የመጡ የኩላሊት፣ የካንሰር መንስኤዎችም አንዱ ምክንያት ሊሆኑ እንደሚችሉ እና አብዛኛውን ወንዞች የአዋሽ ገባር ወንዞች በመሆናቸው አዋሽ ወንዝን በአሁኑ ወቅት ከአገልግሎት ውጭ እንዲሆን ማድረጋቸውን ገልጸዋል፡፡

55. እንዲሁም ከአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በተገኘ ጥናት ከአቃቂ፣ ከጐፋ፣ ከቄራ፣ ከመካኒሳ 1፣ ከመካኒሳ 2 እና ከቤላ አትክልቶች(ጥቅል ጐመንና ሰላጣ) ናሙና ተወስዶ በቤተ-ሙከራ የታየ መሆኑ እና በእነዚህም አትክሎቶች ላይ የታዩ ንጥረ ነገሮች (Electrical Conductivity, Total Nitrogen, COD, BOD, Feacal coliforms) እንዲሁም የከባድ ብረት ይዞታ ከደረጃው በላይ በአትክልቶቹ ላይ መገኘቱ ተገልጿል፡፡

56. በተጨማሪም በባህርዳር በሁለቱ ቆዳ ፋብሪካዎች አባይ ወንዝ ብክለት የደረሰበት በመሆኑ የጓሮ አትክልቱ በቲማቲም፣ ሽንኩርትና በርበሬ የመሳሰሉ ተክሎች ላይ ምርት አለማግኘት ከለር መቀየር እንዳጋጠማቸው እና ከ26 በላይ የሚሆኑ አባወራዎች ከብቶች እንደሞቱባቸው ከደሴ ከተማ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት በተገኘ የቪዲዮ መረጃ የአማራ ቴሌቪዥን ከአካባቢ ከሚኖሩ ገበሬዎች ጋር ባቀረበው ቃለ ምልልስ ለመረዳት ተችሏል፡፡

57. በኦዲት ቡድኑ ሞጆ፣ ኮምቦልቻ፣ ሰበታ፣ ባህርዳር፣ አዲስ አበባ ከተማዎችና ቱሁሌደሬ ወረዳ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የሥራ ኃላፊዎች የወንዞችን ብክለት አስመልክቶ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ፋብሪካዎቹ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተቋቋሙ እና ወንዞችን ተከትለው እንዲሰሩ የተደረገ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት የአካባቢ አያያዝ እቅድ እንዲያዘጋጁ

የማድረግ ሥራ እየተሰራ መሆኑ እንዲሁም አዲስ የሚከፈቱ ፋብሪካዎችም በአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ ዝግጅቱና ትግበራው ላይ ክፍተት በመኖሩ የመጡ ችግሮች መሆናቸውን የገለጹ ሲሆን በተጨማሪም በባህርዳር፣ በአዲስ አበባና በቱሁለደሬ ወረዳ ቆዳ ፋብሪካዎች ላይ እርምጃ የተወሰደና የማሸግ ሥራ ተሰርቶ የነበረ ቢሆንም ከበላይ አካላት ጣልቃ በመግባት እንዲከፈቱ መደረጉንና በአዲስ አበባ የውለታ ግዴታ ገብተው እያመረቱ የፍሳሽ ማጣሪያ እንዲገነቡ የተደረገ ቢሆንም ምርቱ ባለመቆሙ ብክለቱ እንደቀጠለ ገልጸዋል፡፡

58. እንዲሁም በሞጆ ፋብሪካዎቹ የቆዩና ከከተማ ዳር ናቸው ተብሎ ታስቦ የተሰሩ ቢሆንም አሁን ላይ ከተማው ሰፍቶ መሐል መሆናቸውን ሁሉንም መዝጋት እንደማይችሉና እርምጃ ሲወስዱ ወደ ክስ እንደሚሄድ ማስረጃ ለማቅረብም ቤተ ሙከራ አለመኖሩን አስረድተዋል፡፡

59. በተጨማሪም በከተማቸው የጋራ የፍሳሽ ማጣሪያ እንዲሰራ በፌዴራል መ/ቤቱ በውጭ ድርጅት የተጠና ቢሆንም እስከ 200 ሄክታር መሬት የሚያስፈልግ በመሆኑ ከካሳ እና ከቦታ ጋር በተያያዘ ስምምነት ላይ ባለመደረሱ መሰራት አለመቻሉን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም በአማራ ክልል አካባቢ ጥበቃ በአሁኑ ወቅት የባህርዳር ቆዳ ፋብሪካ ሁለተኛው የማከሚያ ግንባታው ሰርቶ ካለፈው የተሻለ መሆኑና ሀበሻ ቆዳ ፋብሪካም በገበያ ምክንያት ማቆሙን አሁን ባለበት ሁኔታም እንዲቀጥል እንደማያደርጉት፤ ኮምቦልቻ አካባቢ ጥበቃ ባለሙያ መ/ቤቱ ተቆጣጥሮ እርምጃ ለመውሰድ የሰው ኃይል የሌለውና የተደራጀ አለመሆኑን፤ በተለይ ሁሃክስ የተባለ የቻይና ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ በማህበረሰቡ ቅሬታ እንደሚመጣ እና ማስረጃ በማስፈለጉ የፍሳሽ ናሙና ለማስመርመር በኮሚሽኑ የተወሰደ ቢሆንም ምላሽ አለመላኩን ገልጸዋል፡፡

60. እንዲሁም የፍሳሽ ማጣሪያ ያላቸው ፋብሪካዎችም ቢሆን ጊዜ ጠብቀው ሌሊት እና መብራት በሚጠፋበት ወቅት ያልታከመ ውሃ እንደሚለቁ ለማሳያ ያህል ሜታ አቦ ቢራ ፋብሪካ የኦዲት ቡድኑ በሰበታ ከተማ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት በተገኘበት ወቅት ሞላሰስ በቦቴ ሞልቶ ወደ ፍሳሽ ቆሻሻ መድፊያ ይዞ ሲሄድ በክትትል እንደተደረሰበትና ለህግ አካላት መሰጠቱን ለማወቅ ተችሏል፡፡

61. ጉዳዩን አስመልክቶ ለኮሚሽኑ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እስከ 2008 ዓ.ም. የማስታመም ሥራ ሲሰራ እንደነበርና በ2010 ዓ.ም. አዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ጋር በመሆን በአዲስ አበባ በሚገኙ የቆዳ ፋብሪካዎች ላይ የማሸግ ሥራ የተሰራ ቢሆንም በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በቃል ትእዛዝ እንዲከፈት መደረጉና ፋብሪካዎቹ ውል ገብተው ሂደት ላይ ሲሆኑ ለወደፊት ጠንከር ያለ እርምጃ እንደሚወስዱ የገለጹ ሲሆን ሞጆ ላይ የጋራ ፍሳሽ ማጣሪያ ጥናት ተጠንቶ ሊገነባ በመታሰቡ ፋብሪካዎቹ ላይ መዘናጋት መፍጠሩን እና የጋራ ፈሳሽ ማጣሪያውን ለመስራት ከተማ አስተዳደርና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የመሬት ርክክብ አለማድረጋቸው፣ በተጨማሪ ሊሰራ የታሰበበት ቦታ ላይ አርሶ አደሩ ለመነሳት ፍቃደኛ አለመሆኑን አስረድተዋል፡፡

62. በመሆኑም ከስምንት አመት በፊትም እነዚህ ኢንዱስትሪዎች ብክለት እያደረሱ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ የተቻለ ሲሆን በሀገራችን ህገ መንግሥት አንቀጽ 44 ላይ ማንኛውም ሰው ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት እንዳለው የሚደነግግ በመሆኑ ፋብሪካዎቹ በሰው ጤናና በእንስሳት ላይ እያደረሱ ካሉት ጉዳት አንጻር እና በአዋሽ ወንዝ ተፋሰስ ውስጥ የሚገኙ የኢንዱስትሪዎች ዓይነትና ብዛትን አንጻር ደረጃቸውን ያልጠበቁ ፍሳሾች ወደ ወንዝ ወይም ፍሳሽ አካላት መለቀቃቸው ወንዞቹ ለአርሶ አደሩ የሚሰጡትን ጥቅም ከማሳጣቱም በላይ ወንዞቹ በተፈጥሮ ሊሰጡ የሚችሉትን ጥቅም እስከመጨረሻው ሊያሳጣ የሚችል ነው፡፡

**ፋብሪካዎች ወደ ሥራ ከመግባታቸው በፊት የአካባቢ ተጽዕኖ**
**ግምገማ ሰነድ ማቅረባቸውንና ሰነዱን ተግባራዊ ማድረጋቸውን በተመለከተ፤**

63. ከኢንዱስትሪዎች ወይም ከፋብሪካዎች የሚወጡ ዝቃጮች ብክለት እንዳያስከትሉ ፋብሪካዎች አስቀድመው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሰነድ እንዲያቀርቡ በማድረግ በሚመለከተው አካል ሊጸድቅ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ እንዲሁም ለማምረቻ ተቋማት ሥልጣን የተሰጠው ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት የሥራ ፈቃድ የሚሰጠው ልቀቱ በካይ አለመሆኑን፣ ከሆነም በአካባቢ ደረጃ ከተፈቀደው ጣራ የማይበልጥ እና ልቀቱ ወደ አካባቢ ቢለቀቅ አደጋ የማያስከትል መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ሊሆን ይገባል፡፡

64. ሆኖም የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 መሰረት ማንኛውም ፍቃድ (ኢንቨስትመንት፣ የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ) ሰጪ መሥሪያ ቤት ፍቃድ ከመሥጠቱ በፊት ከኮሚሽኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንዲሆን የይሁንታ ፍቃድ እንዲያቀርብ መደረጉን አስመልክቶ በተደረገው ማጣራት፡-

- በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልል ኢንቨስትመን ቢሮ፣ ሞጆ፣ አዳማ፣ በባህርዳር፣ ደሴ፣ ኮምልቻ እና ደቡብ ወሎ ዞን ኢንቨስትመንት ቢሮዎች ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፍቃድ ሲወስዱ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ የይሁንታ ፍቃድ እንዲያቀርቡ የማይደረግ መሆኑ፣
- በተመሳሳይ በናሙና በታዩት በሁሉም ንግድ/ሥራ ፍቃድ ሰጪ ተቋማት(ንግድ ሚኒስቴር፣ የአማራ፣ የኦሮሚያ፣ ሞጆ፣ ኮምቦልቻ፣ ባህርዳርና አዲስ አበባ የንግድ ቢሮዎች) ለባለሀብቶች የንግድ ፍቃድ ወይም የሥራ የንግድ ፍቃድ ሲሰጡ ከሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት የይሁንታ ፍቃድ/የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ እንዲያቀርቡ የማይደረግ መሆኑ፣
- በተጨማሪም የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 159/2001 መሰረት ለማምረቻ ተቋማት የሥራ ፈቃድ ሲሰጡ ልቀቱ በካይ አለመሆኑን፣ ከሆነም በአካባቢ ደረጃ ከተፈቀደው ጣራ የማይበልጥ እና ልቀቱ ወደ አካባቢ ቢለቀቅ አደጋ የማያስከትል መሆኑን የማረጋገጥ ሥራ የማይሰሩ እንዲረጋገጥ የማያደርጉ መሆናቸውን ከየመ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ በተሰበሰበ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

65. የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ ያላሰሩ ከአዋጁ በፊት የተቋቋሙ ፋብሪካዎች ከ2001 ዓ.ም. ጀምሮ በአምስት አመት ውስጥ የአካባቢ አያያዝ እቅድ አሰርተው ወደ ተግባር እንዲገቡ የእፎይታ ጊዜ የተሰጣቸው ቢሆንም አብዛኞቹ እቅዱን ያላሰሩ መሆናቸው፣ ለማሳያ ያህል፣ በኦሮሚያ በ2010 ዓ.ም. በ11 ከተሞች በተደረገ ቆጠራ 2150 ፋብሪካዎች ውስጥ 365ቱ/20%/ ብቻ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ወይም የአካባቢ አያያዝ እቅድ ሲኖራቸው የተቀሩት 1780/80%/ የሌላቸው መሆኑንና በአማራ ክልል በደብረታቦር በጎንደርና በቡሬ 211 ፋብሪካዎች ውስጥ 43ቱ/20%/ ብቻ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ/የአካባቢ አያያዝ

እቅድ ያላቸው ሲሆን 168/80%/ቱ የሌላቸው መሆኑ እንዲሁም በአዲስ አበባ ከተማ በናሙና ከታዩ 8 ፋብሪካዎች 6ቱ (በድሬ፣ ባቱ፣ አዲስ አበባ፣ ዋልያ፣ አዋሽ፣ ይርጋለም ጨርቃ ጨርቅ) የሌላቸው መሆኑን ከኦሮሚያ እና ከአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶችና ከአማራ ክልል ኢንዱስትሪ ገበያ ልማት ጽ/ቤት በተገኙና በተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

66. በተጨማሪም በናሙና በታዩት በሁሉም ክልሎች፣ ከተሞች፣ ዞንና ወረዳዎች የመንግሥት ኘሮጀክቶች ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ጨምሮ (አረርቲ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ሁሃጂያን ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ደብረብርሃን ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የአዳማ ኢንዱስትሪያል ፓርክ፣ አራት (4) የተቀናጀ የአግሮፕሮሰሲንግ ኢንዱስትሪ ፓርኮች (ቡልቡላ፣ ይርጋለም፣ ቡሬ እና ባህርዳር) የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሳያሰሩ ወደ ሥራ የገቡ መሆናቸው እንዲሁም ባለሀብቶች ከመንግስት ባንኮች የባንክ ብድር ሲፈልጉ ስለሚጠየቁ ብቻ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ የሚያሰሩ መሆናቸውንና በናሙና በታዩት የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች(ከኦሮሚያ በስተቀር) ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅና ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

67. በሌላ መልኩ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ኖሯቸው ግንዛቤው ባለመኖሩ ሰነዱን ማዘጋጀት ብቻ እንደ ትልቅ ግብ ስለሚቆጥሩት የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ/የአካባቢ አያያዝ እቅድ ያላቸው በናሙና ከታዩት አብዛኛው ፋብሪካዎች (ኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ኮልባ ቆዳ ፋብሪካ፣ ዚንግዛንግና ሀበሻ ቆዳ ፋብሪካ፣ ኢትዮ ጃፓን ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ገላን ቆዳ ፋብሪካ፣ አዋሽ ቆዳ ፋብሪካ፣ ፈሪዳ ቆዳ ፋብሪካ፣ ባለዛፍ አረቄ ፋብሪካ፣ ኮምቦልቻ ቆዳ ፋብሪካ፣ ሁሃክሱ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ጂዶንግ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ አባይ ጣና ምግብ ኮምኘሌክስ) ሰነዱን በፋብሪካቸው የማይገኝና ተግባራዊ የማያደርጉ ሲሆን የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነዱን ወቅቱን ጠብቀው የማያሳድሱ ፋብሪካዎችም (ኮካኮላ ለስላሳ መጠጥ፣ ቢ.ጂ.አይ ቢራ ፋብሪካ፣ የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣) መኖራቸውን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

68. በኦሮሚያ ክልል ኢንቨስትመንት ቢሮ የኢንቨስትመንት ፍቃድ ለመስጠት የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ አንዱ መስፈርት ሆኖ የተቀመጠ መሆኑን በኃላፊው የተገለጸልን ቢሆንም በአዳማ እና በሞጆ የኢንቨስትመንት ቢሮዎች

መስፈርቱ ቢኖርም  የኢንቨስትመንት ውሉ የሊዝ ውል ውስጥ የተካከተ እና የኢንቨስመንት ፍቃድ ባለሀብቱ ካልፈለገ በስተቀር የማይገደድ በመሆኑ በከተሞቹ የመሬት አስተዳደሮች እንደሚጠየቅ ስለሚታሰብ ኢንቨስትመንት ፍቃድ ፈልገው ሲሄዱም የማይጠይቁ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ በሞጆ መሬት አስተዳደር ኃላፊ በበኩላቸው መሬቱን ከማስተር ኘላን እንዲሁም ተመሳሳይ ኢንዱስትሪዎች /በክላስተር/ አንድ ላይ ከማድረግ አንጻር የሚታይ እንጂ አካባቢ ከመጠበቅ አንፃር ትኩረት ተሰጥቶ እንደማይሰራ ኃላፊው አስረድተዋል፡፡

69. በተጨማሪም ሞጆ እና ደሴ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ኃላፊዎች ለኢንቨስትመንት፣ ለንግድና የመሬት ፍቃድ ለሚሰጡ አካላት ፍቃድ ሲሰጡ ባለሀብቶች የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ እንዲያቀርቡ ማድረግ እንዳለባቸው ደብዳቤ የጻፉ ቢሆንም ምላሽ አለማግኘታቸውን በኦዲቱ ወቅት ከየመ/ቤቱ ኃላፊዎችና ለመ/ቤቶቹ በተጻፉ ደብዳቤዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

70. ከላይ የተገለጸውን ጉዳይ አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ለሚመለከታቸው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ኢንቨስትመንት አዋጅ 769/2004 አንቀጽ 30 ቁጥር4/መ  ላይ በተደነገገው መሰረት ስራውን ለመስራት የሚችል ዴስክ በመ/ቤታቸው እንዲያቋቅም የአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ኮሚሽን የጠየቁና የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቱ ውክለና ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መስጠቱ የገለጸላቸው ቢሆንም የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ባለሙያ የለኝም በማለቱ ሥራው እየተሰራ አለመሆኑን ኃላፊዎች አስረድተዋል፡፡

71. የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ኃላፊ በበኩላቸው ጉዳዩን አስመልክቶ በሰጡት መልስ ከውክልናው በኋላ አዋጅ መውጣቱንና የአካባቢ ጥበቃ ኮሚሽን ኃላፊነት በመሆኑ በነሱ ሥራው እየተሰራ አለመሆኑን ገልጸዋል፡፡

72. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ለሚመለከታቸው የኮሚሽኑ ኃላፊዎች ባቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የአካባቢ ጥበቃ ሲቋቋም በሰው ኃይል ያልተጠናከረ በመሆኑ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ ገምግመው እንዲያጸድቁ ለስድስት መ/ቤቶች ውክልና መሰጠቱን እና ውክልናውም በሚኒስትሮች ምክር ቤት መጽደቁን፣ መ/ቤቶቹ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ባለሙያ አሰማርተውና ክፍሉ አደራጅተው እንደሚሰሩ ታሳቢ የተደረገ እና ውክልና ከተሰጣቸው ውስጥ

አምራች ድርጅቶችን በተመለከተ ለኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተሰጠው እና ውክልናውን መቀበሉን ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር 02.38/19 ለኮሚሽኑ በጻፈው ደብዳቤ ለማወቅ የተቻለ ቢሆንም የገመገመውና ያጸደቀው ፕሮጀክት አለመኖሩን  እና በአሁኑ ወቅት ለአስፈፃሚ አካላት ውክልና መሰጠቱ ልክ አለመሆኑን ኮሚሽኑ ተረድቶ ውክልናውን አንስቶ ክፍሉን ለማደራጀት በዝግጅት ላይ መሆኑን  ገልጸዋል፡፡

73. እንዲሁም የመንግስት ፕሮጀክቶችን የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሳያሰሩ በቀጥታ ወደ ሥራ እንደሚገቡ እና ከመንግስት አካላት ጫና መኖሩን በቅርቡ እንኳን ከአዲስ አበባ ከንቲባ ጽ/ቤት የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን በተላከ ደብዳቤ ለመንግሥትና ለግል ፕሮጀክቶች በአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሥርአት እንዲያልፉ የተላለፈው ሰርኩላር በአፈጻጸማቸው ላይ ችግር በመፍጠሩ ሰርኩላሩን ማንሳቱን(የኦዲት ቡድኑ ደብዳቤውን ማየት ችሏል) የሚገልጽ ደብዳቤ ለኮሚሽኑ መድረሱንና  የአካባቢ ጥበቃን አካባቢ ብክለትን በተመለከተ በሚያነሳው ጉዳዮች ላይ እንደ ልማት ጠር የሚቆጠር በመሆኑ አለምአቀፍ ደምበኞች/ገዥዎች/፣ ባንኮች  እና የኮሚሽኑ ባለሙያዎች በግምገማ ወቅት ስለሚያስገድዷቸው አዋሳ ፓርክን ጨምሮ አስቀድሞ መሰራት ቢኖርበትም ወደ ሥራ ከገቡ በኋላ ሰነዱ እንዳሰሩና ከነችግራቸው ወደ ትግበራ እንደገቡ አስረድተዋል፡፡

74. በተጨማሪም በፋብሪካቸው የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማውን የማያስቀምጡና ተግባራዊ የማያደርጉ ፋብሪካዎችን አስመልክቶ በሰጡት ምላሽ የኮሚሽኑ ባለሙያዎች ለክትትል ሲሄዱ ሰነዱ አዲስ አበባ ያለው ቅርንጫፋችን ነው  የሚል ምላሽ የሚሰጡና አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ አሟልተው (የአካባቢ ባለሙያ ቀጥረው፣ የአካባቢ አያያዝ እቅድ አቅደውና በጀት መድበው...) ሰነዱን /የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ/ የማይተገብሩ በመሆናቸው ማዘጋጀቱ ብቻውን ጥቅም አለመኖሩን ገልጸዋል፡፡

75. የኮሚሽኑ ኃላፊ ይህን ይበሉ እንጂ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነዱን ገምግሞ የማጽደቅ ሥራ በአዋጅ የተሰጠው ለኮሚሽኑ በመሆኑና ለአስፈፃሚ አካላትም ውክልና መሰጠቱ ከአሰራር አኳያ ተገቢ ያለሆነ ሲሆን ኮሚሽኑ እራሱ በሰው ኃይል አደራጅቶ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነዱን የማጽደቅ ሥራ ባለመስራቱ

እንዲሁም ፋብሪካዎችን የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማው ከማሰራት በዘለለ አስፈላጊነቱ ላይ ግንዛቤ ሰጥቶ ትግበራው ላይ ጠንካራ ክትትል ባለመኖሩ የአካባቢ ¨ብክለትን የመከላከል ሥራው በአግባቡ እንዳይከናወን በማድረጉ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡

76. ፋብሪካዎች የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ እንዲያቀርቡ የተዘረጋው ስርዓት ተግባራዊ አለመሆኑ ፋብሪካዎች ወደ ሥራ ከመግባታቸው በፊት ከወዲሁ በአካባቢ ላይ ሊደርሱ የሚችሉትን አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተጽእኖን በመለየት አሉታዊ የሆኑትን በመቀነስ ከተቻለም በማሥቀረት ከልማቱ ጎን ለጎን ጤናማ የሆነ አካባቢን ይዞ የማቆየት ሥራው ላይ ችግር የሚፈጥር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**የዝቃጭ ማስወገጃ ወይም ማከሚያ ግንባታዎች በአካባቢ ተጽዕኖ**
**ግምገማ ተቀባይነት ያለውን ደረጃ ተከትለው መሰራታቸውን በተመለከተ፤**

77. በህንፃ ደንቡ መሰረት የሚገነባ  የዝቃጭ ማስወገጃ ወይም ማከሚያ ግንባታ በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ መሠረትና ተቀባይነት ያለውን ደረጃ ተከትሎ የተሰራ ስለመሆኑ አገልገሎት ከመስጠቱ በፊት  በሚመለከተው አካል ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

78. ይሁን እንጂ በናሙና በታዩ በሁሉም የአካባቢ ጥበቃ ኃላፊዎች በቃለ መጠይቅ በተገኘ መረጃ በሚንስትሮች ምክር ቤት ህንጻ ደንብ ቁጥር 243/2003 መሰረት በኢንዱስትሪዎች የሚገነባ  የዝቃጭ ማስወገጃ ወይም ማከሚያ ግንባታ በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ መሠረትና ተቀባይነት ያለውን ደረጃ ተከትሎ የተሰራ ስለመሆኑ የሚረጋገጥበት የአሰራር ሥርዓት አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

79. ህንጻ ደንቡን ለመተግበር ወይም የፍሳሽ ቆሻሻ ግንባታ በአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ መሰረት ለማድረግ የአሰራ ሥርዓት አለመኖሩን አስመልክቶ የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ሥራው ዲዛይን ሲጸድቅ እንዲካተት ከማድረግ ጀምሮ መሰራት የነበረበት ቢሆንም እየተሰራ አለመሆኑና በመ/ቤታቸው ቼክሊስት አዘጋጅተው ለማየት የሞከሩበት ሁኔታ  የነበረ ቢሆንም የጸደቀ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ የማይላክቸው በመሆኑ ሥራውን መስራት እንዳልቻሉና  የአካባቢ ጥበቃ ኮሚሽን የሥራው ባለቤት እንደመሆኑ የአካባቢ

ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ በመላክና ከመ/ቤታቸው ጋር በመወያየት ሥራው እንዲሰራ ሊያደረግ እንደሚገባ አስረድተዋል፡፡

80. ጉዳዩን አስመልክቶ የኦዲት ቡድኑ ለሚመለከታቸው የኮሚሽኑ ኃላፊዎች በቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ከኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር በአመት የመወያያ መድረክ እንዳላቸውና ባለሙያ የማይልኩበት ጊዜ እንደነበር እና የትልልቅ ግንባታዎች የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ እንዲያጸድቁ ውክለና የተሰጣቸው በመሆኑ በዛ መሰረት መሥራት ይችሉ እንደነበር ገልጸዋል፡፡

81. በህንጻ ደንቡ መሰረት የዝቃጭ ማስወገጃ ወይም ማከሚያ ግንባታ እንዲሰሩ የአሰራር ሥርዓት አለመዘርጋቱ በቅርብ የሚቋቋሙ ፋብሪካዎችም የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ ከማዘጋጀት በዘለለ ሰነዱን መሰረት ያደረገና ደረጃውን የጠበቀ የፍሳሽ ማስወገጃ ግንባታ እንዳይኖራቸው ከማድረጉም በላይ ባለሀብቱ የአካባቢ አያያዝ ሥራው ላይ ትኩረት አድርጎ እንዳይሰራ በር ይከፍታል፡፡

## ለ. በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ለሚወገዱ የኢንዱስትሪ ዝቃጭ/ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ ደረጃውን የጠበቀ ስለመሆኑ የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ፤

**በኮሚሽኑ የአካባቢ ብክለት በተመለከተ የወጡ ህጎች**
**ስለመተግበራቸው የተጠናከረ የክትትል ስርዓት መኖሩን በተመለከተ፤**

82. ኮሚሽኑም ሆነ የሚመለከተው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ማንኛውም ሰው ፈቃድ ሳይሰጠው የኢንዱስትሪ ዝቃጭ ያዘለ ፈሳሽ ወይም ጠጣር ነገር ወደ ፍሳሽ መቀበያ፣ ወንዝ፣ ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ እንዳይለቀቅ ወይም እንዳይጣል ቁጥጥር ሊያደርግ እና የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የአካባቢ ብክለት በተመለከተ የወጡ ህጎች ስለመተግበራቸው የተጠናከረ የክትትል ስርዓት ሊኖር ይገባል፡፡

83. ይሁን እንጂ በሚኒስቴር መ/ቤቱ እና በናሙና በታዩ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የአካባቢ ብክለት በተመለከተ ሁሉንም ተደራሽ ከማድረግና ቀጣይነት ባለው መልኩ ከመከታተል አንጻር ጠንካራ የሆነ የክትትል ስርዓት መኖሩን በኦዲቱ ወቅት በተደረገው ማጣራት የሚከተሉት ተገኝተዋል፡-

- የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የአካባቢ ብክለትን ለመከታተል በሚያስችል መልኩ በሰው ኃይል በተገቢ ሁኔታ ያልተደራጁ መሆኑ፣
- በፌዴራል ደረጃ ኢንቨስትመንት ፍቃድ ያወጡና ወደ ሥራ የገቡ ከ2800 በላይ ፋብሪካዎች ቢኖሩም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በ2009 ዓ.ም. 20 እና በ2010 ዓ.ም 30 ፋብሪካዎች ላይ ብቻ ክትትል ያደረገ መሆኑ፣
- በአማራ ክልል የአካባቢ ጥበቃ በ2010 ዓ.ም በ8 ፋብሪካዎች ላይ ብቻ ክትትል ያደረገ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት አብዛኛውን ጊዜ ከማህበረሰብ በሚመጣ ጥቆማ/ቅሬታ መሰረትን ያደረገ ክትትል የሚያካሂድ ሲሆን በ2010 ዓ.ም. እቅድ መሰረት አድርጎ ክትትል ያደረገባቸው ፋብሪካዎች 10 ብቻ መሆናቸው፣
- በኮምቦልቻ በዚህ አመት አንድ ባለሙያ የተጨመረ ቢሆንም ላለፉት አመታት አንድ ባለሙያ ብቻ በመኖሩ  እቅድ መሰረት አድርጎ ሳይሆን ጥቆማ ሲመጣ ብቻ ፋብሪካዎችን የሚያዩ መሆናቸው፣

- በተመሳሳይ በባህርዳር ከተማ ህግ ተከባሪነት ላይ አንድ ባለሙያ ብቻ ያለ በመሆኑና በተጨማሪም በአማራ ክልል ከተሞች የደሴ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቱ ጨምሮ በጽዳትና ውበት ሥር ሆነው ተጠሪነታቸው ለከተማ ልማት በመሆኑ ከክልሉ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ጋር በእቅድም ሆነ በሪፖርት የማይገናኙ በመሆኑ በተዋረድ መሰራት ያለባቸው የክትትል ሥራዎች በአግባቡ እንዳይከናወን ማድረጉ፣ በተጨማሪም በባህርዳር ፍሳሽ ላይ ትኩረት በማድረግ ሆቴሎችና ዩኒቨርስቲዎችንም የሚያዩ በመሆኑ ካለው ውስን የሰው ኃይል አንጻር በሚፈለገው ደረጃ ክትትል አለመኖሩ ከአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ኃላፊዎች ገልጸዋል፡፡

84. እንዲሁም ከከተማ ራቅ ብለው የሚገኙ ፋብሪካዎች ወጥ በሆነ መልኩ ለመከታተል የተሽከርካሪ እጥረት መኖሩ ማለትም ኮምቦልቻ፣ ባህርዳር እና ደሴ ከተሞች፣ ደብብ ወሎ ዞን፣ ቱሉሆራ ወረዳ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ተሽከርካሪ አለመኖሩ፣ ሰበታ፣ አዳማ፣ ሞጆ ከተማና ሎሜ ወረዳ የተሽከርካሪ እጥረት መኖሩን (1 እና 2 ሞተር) ብቻ ያላቸው መሆኑ፣

85. ከከተማ ራቅ ያሉ ፋብሪካዎችን ቀጣይ በሆነ መልኩ ለመከታተል ያመች ዘንድ ሥራው እታችኛው መዋቅር ድረስ ያልተዘረጋ መሆኑ ለምሳሌ ኮምቦልቻ፣ ደሴ፣ ሞጆ እና ሰበታ (ካራና ጀሞ ኮንደሚኒየም ድረስ ሥራው መሰራት ያለበት ቢሆንም) ከተሞች ላይ ብቻ እንጂ መዋቅሩ እስከ ቀበሌ ያለወረደ መሆኑ እንዲሁም በባህርዳር ከ6ቱ ክፍለ ከተማ 2ቱ ላይ በመዋቅር ያልተደራጁ በመሆናቸው የፍሳሽ ማከሚያ ቢኖራቸውም ጊዜ ጠብቀው (አዩኝ አላዩኝ ብለው) የሚለቁ ፋብሪካዎችን በመኖራቸው በድንገት በመሄድ ለመቆጣጠር እና ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመከታተል ችግር እንደገጠማቸው በኦዲቱ ወቅት ከየመ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ከቀረበ በቃለ መጠይቅ ለመረዳት ችለናል፡፡

86. በተጨማሪም በክትትል ወቅት መረጃ ለመያዝ የሚያስችል ካሜራ፣ ፋብሪካው ያለበትን ቦታ ለማወቅ ጂ.ፒ.ኤ.ስ፣ የቢሮ መገልገያ ግብዓት የሌላቸው (ኮምቦልቻ፣ ሞጆ ከተሞችና ሎሜ ወረዳ) የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በመኖራቸው የክትትል መረጃዎች በተደራጀ መልኩ ለመያዝ አለመቻሉ፤ በተጨማሪም በኮሚሽኑ እና በአማራ ክልል የፍሳሽ ብክለትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ቤተ-ሙከራ አለመኖሩ፣ በኦሮሚያ ቤተ-ሙከራ ያለ ቢሆንም በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጥ

ከመሆኑም በላይ ቀለል ያሉ ተንቀሳቃሽ የብክለት መለኪያ መሳሪያዎች /አሲዲቲና ቤዚሲቲ ለመለየት የሚያስችሉ..../ ባለመኖራቸው ከፋብሪካዎች የሚለቀቁ በካይ የሆኑና ደረጃቸውን ያልጠበቁ ፍሳሾን መርምሮ በተጨባጭ/በማስረጃነት አቅርቦ እርምጃ ለመውሰድ መቸገራቸው ማለትም (ቀለም ስለቀየረ ብቻ ብክለት አለ መባል የለበትም የሚሉ ፋብሪካዎች መኖራቸው)፣ በተጨማሪም ለከተሞች፣ ለዞንና ለወረዳ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በፌዴራል እና በክልል ደረጃ ፍቃድ የሚወስዱ ፋብሪካዎች የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ በግልባጭ የማይላክላቸው በመሆኑ ሰነዱን መነሻ አድርገው ለመከታተል መቸገራቸው ለየመ/ቤቱ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ እና ከተከተለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

87. በተጨማሪም የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ/የአካባቢ አያያዝ እቅድ ያላቸውና የሌላቸውን በመለየትና ተከታትሎ የአካባቢ አያያዝ እቅድ እንዲያዘጋጁ የማድረግ ሥራ በኦሮሚያ የተሻለ ቢሆንም በአማራ ክልላዊ መንግስት 1,655 ፋብሪካዎች ላይ ታቅዶ 700 ፋብሪካዎች/42%/ ላይ ብቻ መሰራቱ እና በአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ሥራው እየተሰራ አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከክልሉና ከከተማው አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት የ2010 እቅድ አፈጻጸም ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

88. በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 21 ፋብሪካዎች በክትትሉ መሰረት ግብረ መልስ የማይሰጣቸው መሆኑ ሆኖም ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግንዛቤውን ያገኙ እንደመሆናቸው መንግስት ለወደፊቱ የፍሳሽ ቴክኖሎጂውን እና ማከሚያ ኬሚካሎቹን በቀላሉ የሚሰሩበትንና የሚያገኙበትን መንገድ እንዲያመቻች ወይም መፍትሔ እንዲሰጥ መንግስት ድጋፍ ሊያደርግ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

89. ከላይ የተገለጹ ጉዳዮችን አስመልክቶ በክልሎች ያሉ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ የኦሮሚያ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት የሰው ኃይል በክልሉ ጠቅላላ በመዋቅር ከተፈቀደው አንፃር ያለው የሰው ኃይል 22 በመቶው ብቻ መሆኑ የባለሞያ እጥረት መኖሩ እና ፍሳሾችን ደረጃውን የጠበቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ቤተ ሙከራው(Labratory) ከአለፈው አመት ጀምሮ በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት አስፈላጊ እቃ ግዥ ማድረግ ባለመቻሉና ባለሙያ ባለመኖሩ ሥራው መቆሙን አስረድተዋል፡፡

90. እንዲሁም በአማራ ክልል የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት በከተሞች የሚገኙ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ተጠሪነታቸው ለክልሉ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት መሆን ሲገባቸው ለከተማ ልማት ኮንስትራክሽን መ/ቤት በመሆኑ ሪፖርት እንደማይደርሳቸው፣ አስቀድሞም በመሬት አስተዳደር ሥር እንደነበሩ እና መ/ቤታቸው በቀጥታ ሳይሆን በሌላ አካል ዞሮ የሚያገኛቸው በመሆኑ በጋራ አቅደው እንዳይተገብሩ እንቅፋት እንደሆናቸው ገልጸው የክልሉ ቤተ-ሙከራን(Labratory) አስመልክቶ በአሁኑ ወቅት ለማቋቋም አንድ ኬሚስት መቀጠሩንና ዝግጅት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም መ/ቤቱ እንደክልል በባለስልጣን ደረጃ የተቋቋመው ሁለት አመቱ በመሆኑ በቂ የሰው ኃይል እንዳልነበረና አሁን ግን የተሻለ በመሆኑ በተወሰኑ ፋብሪካዎች ላይ መሻሻል መኖሩን ሁሉም ላይ ከብቃትም ሆነ ከቁጥር አንፃር የሰው ኃይሉ ቢጠናከር የክትትል ሥራው ጥሩ እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡

91. የኮሚሽኑ ኃላፊዎች ስለጉዳዩ በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ በክፍሉ ከሚሰሩት ሥራዎች አንጻር ያለው የሰው ኃይል አነስተኛ በመሆኑ ትኩረት አድርገው ክትትል የሚያደርጉት ወይም የሚያዩት ችግር ያለባቸውን ፋብሪካዎች መሆናቸውንና በክፍሉ የተሽከርካሪና ከሰው ኃይል ችግር በመኖሩ ሁሉንም ማዳረስ አለመቻላቸውን፤ በክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች እስከ 6000 ፋብሪካዎች እንደሚታዩ ገልጸው ግብረ መልስ መላክን አስመልክቶ በኮሚሽኑ የታዩ ፋብሪካዎችን ግብረ መልስ በኩል ፋብሪካዎች ለእርምጃ እንዲያመች በክልሎችና በከተማ አስተዳደሮች እንደሚልኩና በነሱ በኩል እንደሚደርሳቸው ታሳቢ እንደሚደረግም ገልጸዋል፡፡ የክልል አደረጃጀትን በተመለከተ ተነባቢ የሆነ አደረጃጀት እንደሌለና በትግራይ ክልልም በከተማ ደረጃ አለመኖሩን፣ በክልሎች ከተሞቹ በከንቲባ የሚመሩ ስለሆነ የማደራጀት ስልጣን የኛ ነው የሚል መልስ እንደተሰጣቸው አስረድተዋል፡፡ ሆኖም ግን አዋሳ በከንቲባ ሥራ ቢሆንም ለብቻ ዴስክ እንዳለውና በዚህ መልኩ ሌሎችም መሄድ እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡

92. የኮሚሽኑ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች እስከታችኛው የቀበሌ መዋቅሮች ቢዋቀሩ፤ ተጠሪነታቸው ለክልላቸው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ቢሆንና በሁሉም ተመሳሳይ መዋቅር እንዲኖር ስላለው ጠቀሜታና ጉዳት በማሳየት ከከተሞቹ ከንቲባዎች ተወያይቶ ስለመፍታቱ፤ ኮሚሽኑ በራሱ፣ ክልሎች፣ ከተሞችና ወረዳዎች በአግባቡ እንዲደራጁ የተደረገ ጥረት በኦዲቱ ወቅት ማየት ስላልተቻለ

እንደሁም ኮሚሽኑን ጨምሮ መ/ቤቶቹ  በአዋጅ የተሰጣቸውን ስልጣንና ተግባር ለመፈፀምና ከመ/ቤቶች  ሊገኝ የሚችለውን ከብክለት የጸዳ አካባቢን የመፍጠር ሀገራዊ  ጠቀሜታ በቅልጥፍናና ውጤታማ በሆነ አሰራር ለማግኘት እንዲቻል በተሟላ የሰው ኃይልና ድርጅታዊ አቅም ካልጎለበተ በስተቀር የተቋቋሙበት አላማ ሊሳካ የማይችል መሆኑ ሊታወቅ ይገባል፡፡

93. በመሆኑም የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ለክትትል በሚያመች ደረጃ እስከታችኛው መዋቅር ድረስ ባለመደራጀታቸውና በሰው ኃይል ሆነ በግብዓት ተጠናክረው ክትትል ባለማድረጋቸው አካባቢ ብክለትን ለማስቀረት በሚደረገው የክትትል ሥራው ጠንካራ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ ፋብሪካዎች ፍቃድ ሳይሰጣቸው የፍሳሽና ጠጣር ቆሻሻዎችን ወደ ውሃ መውረጃ ትቦዎች፣ ወንዞች … በመጣል አካባቢና ማህበረሰቡን እንዲበክሉና አካባቢ ህግ የማስከበር ሥራው ላይ ተጽእኖ ፈጥሯል፡፡

**ፋብሪካዎች በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለማስተካከል**
**<u>እና ችግሮችን ለመፍታት እርምጃ መወሰዱን በተመለከተ፤</u>**

94. ኮሚሽኑ ወይም የሚመለከታቸው የክልል/የከተሞች የአካባቢ መሥሪያ ቤቶች የኢንዱስትሪ ቆሻሻ አወጋገድ ዙሪያ ከማህበረሰቡ የሚመጡ ቅሬታዎችን የሚፈቱበት የቅሬታና አቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት ሊዘረጉ ይገባል፡፡

95. እንዲሁም በጤና ወይም በአካባቢ ላይ አደጋ እንዳያስከትል ከሚያሰጋ የሥራ እንቅስቃሴ ሊመጣ የሚችል ጉዳትን ለመከላከል ድርጅትን እስከ መዝጋት ወይም ወደ ሌላ ቦታ እስከ ማዛወር የሚደርስ ማንኛውንም አስፈላጊ እርምጃ ሊወስዱ ይገባል፡፡

96. ይሁን እንጂ በኮሚሽኑም ሆነ በናሙና በታዩ በአዲስ አበባ ከተማ፣ በኦሮሚያና በአማራ ክልል ከከተለያዩ አካላት የሚመጡ ቅሬታዎች ቅሬታ አቀራረብ ስርዓት የተዘረጋ ቢሆንም የቅሬታ አፈታት መመሪያ አለመኖሩ፣


97. በኢንዱስትሪ ብክለት መከላከያ ደንብ ቁጥር 159/2001 ብክለትን አስመልክቶ ከማህበረሰቡ የሚመጡ ቅሬታዎች የቀረበለት የአካባቢ መሥሪያ ቤት ጉዳዩን በማጣራት የወሰደውን እርምጃ በ90 ቀናት ውስጥ ለአቤቱታ አቅራቢው ማሳወቅ እንዳለበት የሚገለጽ ቢሆንም እርምጃ የማይወሰድ እና ከላይ በሪፖርት ቁጥር 46

ላይ የተገለጹ አብዛኛው ፋብሪካዎች ከ2007 ዓ.ም. ጀምሮ ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸውና የብክለት መጠናቸው እየቀነሰ ያልመጣ ቢሆንም ከማስጠንቀቂያ በዘለለ እስከ ሰኔ ወር 2010 ዓ.ም ድረስ ምንም አይነት እርምጃ አለመወሰዱን ከተከለሱ መረጃዎች/ለፋብሪካዎች በተላከ ደብዳቤ/ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለምሳሌ፡-

- በሞጆና በአዲስ አበባ ከተሞች፣ በደቡብ ወሎ ዞን ተሁለደሬ ወረዳ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ፋብሪካዎች ላይ የማሸግ ሥራ ሲሰሩ በበላይ አካላት (ከየከተሞቹ ከንቲባ ጽ/ቤት፣ ክክልል አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን) ጣልቃ ገብነት በአዲስ አበባ 6 እና በሞጆ 12 ቆዳ ፋብሪካዎች እስከ ሦስተኛ ደረጃ ማከሚያ እንዲገነቡ በጊዜ የተገደበ የግዴታ ውል እንዲገቡ ተደርጎ የተከፈቱ ቢሆንም ብክለቱ መቀጠሉ፣
- በሰበታ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት በሀፋዳ እና ብሉ ናይል ቆዳ ፋብሪካዎች ከ2009 ዓ.ም. አጋማሽ ጀምሮ ርጥብ ቆዳ እስከብሉ ኘሪንት ድረስ ያለውን እንዳያመርቱ የታገደ ቢሆንም አይካ አዲስ፣ ጂንዶንግ ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካእና ባለዛፍ አረቄ ፋብሪካ የመሳሰሉት እየበኩሉ የሚገኙ በመሆኑ ወንዞች ላይ ያለው ብክለት መቀጠሉ፣
- በደሴ ከተማ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ከህብረተሰቡ በሚቀርብ ቅሬታ መሰረት በተደጋጋሚ ለፋብሪካዎች ማስጠንቀቂያ የሚሰጥ ሲሆን አልፎ አልፎ ወደ ህግ ቢሄዱም ማስተካከያ የማያደርጉ ፋብሪካዎች መኖራቸውን የየመ/ቤቱ ኃላፊዎች ገልጸዋል ለማሳያ ያህል፡-
    - ገራዶ የዶሮ ፋብሪካ ቅሬታ ቀርቦበት ክስ ከተመሰረተበት በኋላ የክሱ ውሳኔ ሳይሰጥ በድጋሚ ሌላ ቦታ ላይ የዶሮ ሥጋ ማቀናበሪያ በከተማ መስተዳድር በመሰጠቱ ህዝቡ በራሱ እርምጃ በመውሰድ ድርጅቱን ላይ ጉዳት ማድረሳቸው፣
    - የደሴ ከተማ ቄራ ፋብሪካን በተመለከተ ከ40-50 በሬ የሚታረድና ፍሳሹ ሳይታከም እንዳለ ደሙ በቦይ የአካባቢ መንደር መሀል ለመሀል ሰንጥቆ ወደ ወንዝ የሚገባ እና በተጨማሪ በእርዱ ወቅት የሚወጡ ቆሻሻዎችንም(ማለትም የበሬ እግር፣ ሆድ እቃ ወዘተ) ከፋብሪካው 50 ሜትር እርቀት ላይ ባለ ወንዝ ላይ የሚጥል እና በነዋሪው ከፍተኛ ቅሬታ የደረሰ ቢሆንም በከተማ መስተዳደሩ የበፊቱ ፈርሶ እዛው ቦታ ላይ በአለም ባንክ ገንዘብ በዘመናዊ መልክ ቄራ ሊሰራ በመታሰቡ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቱ ከከተማ መስተዳደሩ ጋር ቦታ መቀየር እንዳለበት በመነጋገር የግንባታውን ሥራ ካስቆመ አምስት

አመት የሆነው ቢሆንም የሥጋ ማምረቱን የቀጠለና ካለምንም የማከም ሥራ ፍሳሹን የሚለቅ በመሆኑ ብክለቱ የቀጠለ ሲሆን ህዝቡ አሁንም ቅሬታ እያቀረበ እንደሆነ የኦዲት ቡድኑ ቦታው ላይ በመሄድ በመስክ ምልከታና ከአካባቢው ማህረበሰብ በተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

## ምስል 8 ደሴ ቄራ ፋብሪካ በበሬ እርድ ምክንያት የሚለቀው ፍሳሽ



98. ስለጉዳዩ በናሙና በታዩ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን መ/ቤቶች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስና በተከለሱ ማስረጃዎች፡-

- በሰበታ፣ አዲስ አበባ፣ ሞጆ፣ ባህርዳር  በካይ የሆኑ ፋብሪካዎች(ቆዳና ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካዎች) አስቀድመው  ከከተማ ውጭ ነው ተብሎ ቦታ የተሰጣቸው ቢሆንም በአሁኑ ወቅት ከተሞቹ እየሰፉ መጥተው በመኖሪያ ቤቶች መሐል በመሆናቸውና ወንዝ ተከትለው እንዲሰሩ በመደረጋቸው የአካባቢ ማህበረሰብ የቅሬታ ምንጭ እንደሆኑ፣
- በተጨማሪም ፋብሪካዎቹን ለመዝጋት ከ1000 በላይ ሰራተኛ ያላቸው በመኖራቸው ሰራተኞችና ቤተሰቦቻቸው ላይ ሊመጡ የሚችሉ ችግሮችን በማሰብ፣ ወደ ሌላ ቦታ ለማዘዋወርም የተዘጋጀ ቦታ የሚያስፈልግ በመሆኑ፣ በጥናትና በማስረጃ የተደገፈ ሥራ ለመስራት ቤተ ሙከራ ባለመኖሩ፣ የፍትህ አካላት የጉዳቱ መጠን ምን ያህል እንደሆነ ግንዛቤ  እጥረት በመኖሩ  እና ባለሀብቱም ምርት ላይ እንጂ አካባቢን ብክለትን በተመለከተ ተጠያቂነት

አለብኝ የሚል አመለካከት ዝቅተኛ በመሆኑ አብዛኞቹ ፋብሪካዎች ላይ የማስተማርና ማስጠንቀቂያ የመስጠት ሥራ እንጂ ገፍተው ሄደው የማገድና የማሸግ ሥራዎች አለመሰራታቸው ገልጸዋል፡፡

- በአማራ ክልል እንደ ክልል አስፈፃሚ አካላት ትኩረት ያለመስጠትና ጥቆማ ሲሰጥ ያለመተባበር ችግር መኖሩን ገልጸው በአሁኑ ወቅት ደንብ 001/2010 ተዘጋጅቶ መጽደቁን ነገር ግን እስከአሁን ተግባራዊ አለመደረጉ፣
- በኦሮሚያ ክልል እንደ ህጉ ከሆነ አብዛኛዎቹ ፋብሪካዎች ሊዘጉ የሚችሉ ቢሆንም እስከ 5000 ሰራተኛ ያላቸው መኖራቸውንና እንደ ሀገር የማስታረቅ ሥራ መሰራት እንዳለበት፣ በመንግስትም ልማት እንደማደናቀፍ የሚቆጠር በመሆኑ እና ሞጆ ላይ 12 ፋብካዎች የፍሳሽ ማከማያውን ገንብተው የሚጨርሱበትን እቅድ አቅረበው የውለታ ግዴታ ገብተው እያመረቱ መሆኑን ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ከአቅም በላይ የሆኑ 18 ፋብሪካዎችን መዝጋታቸውን አስረድተዋል፡፡

99. ከላይ ስለተገጹት ጉዳዮች የኮሚሽኑ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በተሰጠው መልስ እርምጃ ለመውሰድ የአፈፃፀም መመሪያ ባይኖርም በደንቡ መሰረት መስራት መቻሉን እና የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ሥራቸው የፋብሪካ መረጃዎችን እርምጃ እንዲወሰድ ለፖሊስ ማቅረብ መሆኑን እና የመመሪያ ችግር ሳይሆን ፋብሪካዎችን መዝጋት ብዙ ሰራተኛን ከሥራ ማፈናቀል ይሆናል በሚል አስተማሪ በሆነ መልኩ ማስጠንቀቂ የመስጠትና የማስታመም ሥራ ስለሚሰራ እና ፋብሪካዎች የሥራ እድሉን እንደማስተማመኛ የሚቆጥሩትና መንግስት ጨክኖ የሚዘጋም ስለማይመስላቸው ፈጥኖ የማስተካከል ሥራ አለመኖሩንና ከአለፈው አመት ጀምሮ የታሸጉ ፋብሪካዎች መኖራቸውንና በቀጣይ እርምጃ የመውሰድ ሥራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸው የመንግስት ጣልቃ ገብነትን በተመለከተ በአዲስ አበባ ቆዳ ፋብሪካዎች ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በቃል በመጣ ትእዛዝ መክፈታቸውን ገልፀዋል፡፡

100. የኮሚሽነሩ ኃላፊዎች ይህን ይበሉ እንጂ አካባቢን እና ድንበር ተሻጋሪ ወንዞችን በመበከል በሚሊዮን የሚቆጠረውን የህብረተሰብ ክፍል ላይ ጉዳት በማድረስ እና ለመመለስ አስቸጋሪና ብዙ ጊዜ የሚፈጅ ምናልባትም መመለስ የማይችል የአካባቢ ምህዳርን መስዋዕት በማድረግ እንደምክንያት ያቀረቡት ጉዳይ ፋብሪካዎች

እንደሀገር እያደረሱ ያለው ጉዳትና የሚስገኙትን ጥቅም በማነፃፀር(cost benefit analysis) በጥናት ተደግፎ የቀረበ ባለመሆኑ የሰጡትን ምክንያት አልተቀበልነውም፡፡

101. በመሆኑም በደንቡ መሰረት ፋብሪካዎቹ ላይ እርምጃ ባለመወሰዱ ፋብሪካዎቹ ትኩረት ሰጥተው የማስተካከሉን ሥራ እንዳይሰሩ እና ብክለቱ እንዳይቀንስ በማድረግ በወቅቱ የማህበረሰቡ ቅሬታ ያልተፈታ ከመሆኑም በላይ ብክለቱ መጠንና ደረጃ በጥናት ሳይለይ ነገር ግን በሰው ጤና እና በአካባቢ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ መሆኑ እና የማይተኩ የተፈጥሮ ሀብቶችና ምህዳሮችን እየጎዳ ይገኛል፡፡

**ኮሚሽኑ ኢንዱስትሪ /ዝቃጮች/ ቆሻሻዎች አወጋገድ**
**ችግሮች እና መፍትሔዎች ላይ ጥናት ማጥናቱን በተመለከተ፤**

102. ኮሚሽኑ እንደሀገር በፌዴራልም ሆነ በክልል የሚወገዱ የኢንዱስትሪ ዝቃጮች ወይም ቆሻሻዎች ስለአወጋገዳቸውና ስለሚያስከትሉት/ስላስከተሉት ችግሮችና የጉዳት መጠን እንዲሁም መፍትሔዎቹ በማጥናት ተግባራዊ እንዲሆን ሊሰራ ይገባል፡፡

103. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች እንደታየው በኮሚሽኑ እና በአማራ ክልል የተጠና ጥናት አለመኖሩ፣ በኦሮሚያ ክልል አንድ የደሰሳ ጥናት ቢኖርም ዝቃጮቹ ስላደረሱት ጉዳት የሚያሳይ ጠለቅ ያለ ጥናት አለመሆኑ እና በአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ቆየት (ከዘጠኝ አመት በላይ የሆኑ)ያሉና የኢንድስትሪ ዝቃጭ በወንዞችና በአትክሎቶች ላይ ያስከተሏቸውን ብክለት አስመልክቶ የተጠኑ ጥናቶች ያሉ ሲሆን ጥናቶች ለወደፊት በሰው ጤናና በእንስሳት ላይ ያደረሱትን ጉዳት አስመልክቶ ሌላ ጥልቅ የሆነ ጥናት መካሄድ እንዳለበት የጠቆሙ ቢሆንም በተጨባጭ እስካሁን ስለአደረሱት ወይም ሊያደርሱት ስለሚችሉት ጉዳት መጠን የተጠና ጥናት አለመኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

104. ጉዳዩን አስመልክቶ የኮሚሽነሩ የሥራ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ለነባር ፋብሪካዎች የተሰጠው የእፎይታ ጊዜ ሲያልቅ ማምረቻ ተቋማቱ በምን ደረጃ እንዳሉ ማየታቸውን እና በየጊዜ የተጠኑ ጥናቶች መኖራቸውን ነገር ግን በጥልቀት ይህን ያህል ጉዳት ደርሷል የሚል ጥናት ግን አለማጠናቱን ገልጸዋል፡፡

105. በመሆኑም የኢንዱስትሪ ቆሻሻ አወጋገድ ስለሚያደርሱት ጉዳት ጥናት ባለመኖሩ በግምት ከመናገር በዘለለ መንግስትም ሆነ ፋብሪካዎች እያደረሱ ስላለሉት ጉዳት መጠን ግንዛቤው ኖሯቸው በቀጣይ ሊወሰዱ የሚገባቸው ጉዳዮችን በመለየት መፍትሔዎች ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ የራሱ አስተዋጽኦ ሊኖር የሚችል በመሆኑ ጥናቱ አለመጠናቱ ችግሩ በአግባቡ እንዳይታወቅ አድርጎታል፡፡

<u>ኮሚሽነሩ ፋብሪካዎች የአካባቢ አያያዝ መቆጣጠሪያ ዘዴ/ሥርዓት መኖሩ</u>
<u>እና የአካባቢ የውስጥ ኦዲት ማስደረጋቸውን ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤</u>

106. በደንብ ቁጥር 159/2001 መሰረት ፋብሪካዎች በኢንዱስትሪ ዝቃጭ አወጋገድ ላይ የወጡ ድንጋጌዎች መከበራቸውን የሚያረጋግጡበትን የውስጥ የአካባቢ አያያዝ መቆጣጠሪያ ዘዴ ሊያዘጋጁ እና የአካባቢ የውስጥ ኦዲት በማድረግ ሪፖርቱን በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ መሰረት ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ሊልኩ ይገባል፡፡

107. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በናሙና ከታዩት 42 ፋብሪካዎች ውስጥ የአካባቢ አያያዝ መቆጣጠሪያ ዘዴ/ሥርዓት (በጀት መመደብ፣ ፖሊሲ፣ አሃድ፣ የአካባቢ ባለሙያ መቅጠር፣ የአካባቢ አያያዝ እቅድ በማቀድ ወደ ተግባር መግባት ወዘተ) የዘረጉት 10 (24%) ፋብሪካዎች ብቻ ሲሆኑ የተቀሩት 32ቱ /76% / የአካባቢ የአያያዝ ሥርዓት ባለሞያ (የአካባቢ ባለሙያ) የሌላቸው ወይም በከፊል ያላቸው መሆኑ ከፋብሪካዎች ከተገኙ ማስረጃዎች እና ከኮሚሽኑ የክትትል ሪፖርት ለማወቅ ተችሏል፡፡

108. በተጨማሪም ብክለትን ለመከላከል የወጣ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 159/2001 መሰረት ፋብሪካዎች የደንቡን ድንጋጌዎች እንዴት እየተገበሩ እንደሆነ የሚገልጽ የአካባቢ የውስጥ ኦዲት አስደርገው ስልጣን ለተሰጠው የአካባቢ መ/ቤት መረጃ ማቅረባቸውን በተመለከተ በተደረገው ማጣራት የሚከተሉት ታይተዋል፡-

- በናሙና ከታዩት ፋብሪካዎች ውስጥ “ISO” ሰርተፊኬት ለማግኘት ኦዲት ከሚያስደርጉ ጥቂት ፋብሪካዎች (ማለትም ኢትዮ ቆዳ ፋብሪካ፣ ቢ.ጂ.አይ ቢራ ፋብሪካ፣ ኮካኮላ ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ) በስተቀር የተቀሩት ፋብሪካዎች ኦዲት የማያስደርጉ መሆኑ፣ እንዲሁም የአካባቢ ኦዲት የሚያስደርጉትም ቢሆኑ

በአማራና ኦሮሚያ ክልል የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤትም ሆነ ለኮሚሽኑ የማይልኩ መሆናቸው፣

- በአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት በ2010 ዓ.ም. 35 ፋብሪካዎች የአካባቢ የውስጥ ኦዲት ሪፖርት እንዲያቀርቡ ለማስደረግ ቢያቅድም ከአራት ፋብሪካዎች በስተቀር/ንፋስ ስልክ ቀለም ፋብሪካ፤ ብሄራዊ አልኮልና አረቄ ፋብሪካ እና ካዲስኮ ቀለም ፋብሪካ፤ ድሬ ቆዳ ፋብሪካ፣/ የተቀሩት የማያስደርጉ ወይም /ለመ/ቤቱ የማይልኩ መሆናቸው፣ በተቀሩት በናሙና በታዩት ከተሞች ፋብሪካዎች ኦዲት የማያስደርጉ ወይም ሥራው ያልተለመደ መሆኑ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ፋብሪካዎቹ የአካባቢ ኦዲት አስደርገው እንዲልኩ ክትትልና ቁጥጥር የማያደርጉ መሆኑ፤

109. በሌላ መልኩ በናሙና በታዩት በሁሉም የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በራሳቸው ፋብሪካዎቹ ላይ የአካባቢ/የክዋኔ ኦዲት እንደማያደርጉ ለየመ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ከቀረበ በቃለ-መጠይቅ እና ከተከለሱ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

110. ስለጉዳዩ በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች፣ ደሴ፣ ሞጆ፣ ሰበታ፣ አዳማ፣ ባህርዳርና ኮምቦልቻ ከተሞችና ደቡብ ወሎ ዞን በሚገኙ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ፋብሪካዎች በ2001 ዓ.ም. በደንቡ መሰረት የአካባቢ አያያዝ መቆጣጠሪያ ዘዴ/ሥርዓት ለመዘርጋት ዝግጅት እንዲያደርጉ የእፎይታ ጊዜ የተሰጣቸው ቢሆንም ጥቂት ፋብሪካዎች ጅምር ሥራ ቢኖራቸውም አብዛኞቹ ያልተጠቀሙበትና ሥርዓቱን ያልዘረጉ መሆኑን ገልጸው፣ ፋብሪካዎች የአካባቢ የውስጥ ኦዲት በማድረግ ሪፖርት ማቅረብን በተመለከተ ግንዛቤው እንደሌላቸውና ተከታትሎ ወደ ሥርዓት ለማስገባት በነሱ በኩል የሰው ኃይል እጥረት ስላለባቸው ሥራውን አለመስራታቸውን አስረድተዋል፡፡

111. ጉዳዩን አስመልክቶ የኮሚሽኑ ኃላፊዎች ለኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ለክትትል ፋብሪካዎች ላይ ሲሄዱ የአካባቢ የውስጥ ኦዲት ማድረግ እንዳለባቸው እንደሚገልጹላቸውና የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት መዘርጋት ላይ ፋብሪካዎች ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ አለመሆኑን አስረድተዋል፡፡ በተጨማሪም ኮሚሽኑም ሆነ የተቀሩት የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የአካባቢ ኦዲት አለማድረጋቸውን አስመልክቶ የኦዲት ማንዋል እየተዘጋጀ ስለሆነ ለወደፊት

ኮሚሽኑም ሆነ ሌሎች የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች በማንዋሉ መሰረት ሥራውን እንዲሰሩ እንደሚደረግም ገልጸዋል፡፡

112. በመሆኑም ፋብሪካዎች የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት እንዲዘረጉ ክትትልና ቁጥጥር ባለመደረጉ ፋብሪካዎች አስቀድመው ብክለትን እንዳያደርሱ የመከላከል ሥራ እንዳይሰሩ አድርጓል፡፡ እንዲሁም በአካባቢ የውስጥ ኦዲት ሥራውም ፋብሪካዎች አሰራራቸውን ገምግመው ለወደፊት የማስተካከልጸ አካባቢን የመጠበቅ ኃላፊነታቸውን እንዳይወጡ ተጸዕኖ ከመፍጠሩም በላይ የችግሩን አሳሳቢነት የሚመጥን የኦዲትና የክትትል ስራ በሚመለከታቸው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶችም ጭምር እንዳይሰራ አድርጓል፡፡

## ሐ. መ/ቤቱ ከኢንዱስትሪ ዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ ጋር በተያያዘ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን፣ እንዲሁም የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤

**ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር**
**<u>ጠንካራ የሆነ ቅንጅታዊ አሰራር መኖሩን በተመለከተ፤</u>**

113. ኮሚሽኑ ወጥ አደረጃጀት በመፍጠር፣ ቅንጅታዊ አሰራርን በማጠናከር ከክልል አካባቢ መ/ቤቶችና እንዲሁም አግባብ ካላቸው ሌሎች መ/ቤቶች ጋር ድጋፍ በማድረግና የጋራ እቅድ በማውጣት በቅርበት ሊሰራ በተጨማሪም ከአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የኢንዱስትር ቆሻሻ ማስወገጃ መገልገያዎችን መገምገምና በአጥጋቢ ሁኔታ መሟላታቸውን በማረጋገጥ አስፈላጊው እርምጃዎችን ሊወስድ ይገባል፡፡

114. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱ ማስረጃዎች እና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች የሚከተሉት ታይተዋል፡-

- ከኢንዱስትሪ ዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ ጋር በተያያዘ ኮሚሽኑ ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ የሆነ ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖሩ፤ ለምሳሌ ከፍቃድ ሰጪ አካላት ጋር (ኢንቨስትመንት ፍቃድ፣ ንግድ ሥራ ፍቃድ፣ የሥራ ፍቃድ) በአካባቢ ጥበቃ ተጽዕኖ ግምገማ አዋጅ ላይ ፍቃድ ሲሰጡ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ሊጠይቁ እና ፋብሪካዎች ሲታገዱ ወይም ሲዘጉ ፍቃዱን ማገድ የሚገባቸው ቢሆንም ሰነዱን የማይጠይቁና የሥራ ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን እንዲሁም ከፍትህ አካላት በአካባቢ ሕግ ተከባሪነት ተሳትፎና ዝግጁነት አነስተኛ መሆኑ፣
- ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር የጋራ እቅድ ቢኖርም በእቅድ መሰረት እየተሰራ አለመሆኑንና በተናጠል የራሳቸውን ድርሻ ለመሥራት የሚጥሩና አፈፃፀማቸውንም ሪፖርት ለኮሚሽኑ ቢልኩም በተጠናከረ መልኩ በጋራ ችግሮች እየታዩና እየተፈቱ እየሰሩ አለመሆናቸውንና ከኮሚሽኑ ጋር ግንኙነታቸው ጠንካራ ነው ማለት የማይቻልና የአካባቢ ጉዳዮችን በተመለከተ ኮሚሽኑ ሥልጣኑ በአዋጅ የተሰጠው በመሆኑ እንደባለቤት

የማስተባበር ሥራውን መሥራት እንዳለበት የየመ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች በኦዲቱ ወቅት ገልጸዋል፡፡

- በተጨማሪም ኮሚሽኑ ከአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ጋር በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ የሆነ አደረጃጀት እንዲኖር በእቅዱ የያዘ ቢሆንም ከክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ጋር ወጥ እና ተናባቢ ያልሆነ አደረጃጀት መኖሩን እና በተወሰኑ ክልሎች በተሟላ ሁኔታ ከክልል እስከ ታችኛው የአስተዳደር እርከን ባለመውረዱ እቅድና አፈፃፀም ላይ ክፍተት መፍጠሩ፣
- እንዲሁም ከሚመለከታቸው የክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት እና አግባብ ካላቸው ሌሎች መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የኢንዱስትሪ ቆሻሻ ማስወገጃ መገልገያዎችን በመገምገም በአጥጋቢ ሁኔታ መሟላታቸውን የማረጋገጥ(ካሊብሬት) ሥራ አለመከናወኑ ከየመ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ከቀረበ ቃለ መጠይቅ እና ከተከለሱ መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

115. ጉዳዩን አስመልክቶ በኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በተሰጠው መልስ አካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ እንዲያጸድቁ ውክልና ከተሰጣቸው አካላት ጋር በየሩብ ዓመቱ የሚገናኙ ሲሆን ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ሰራተኛ ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከህዳር ወር 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ባለሞያ መመደባቸውን ገልፀዋል፡፡ ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የአካባቢ ተፅእኖ ግምገማ ባለሞያ ተመድቦ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት የተቋረጠ መሆኑ፤ እንዲሁም ከክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤች ጋር አደረጃጀቱ ወጥ ለማድረግ የኮሚሽኑም አደረጃጀት የሚለዋወጥና በአሁኑ ወቅትም በድጋሚ የተቀየረ በመሆኑ መቸገራቸው፣ በክልሎች ከተሞች በከንቲባ የሚተዳደሩ ሲሆን የማደራጀት ሥራው የኛ ሥልጣን ነው የሚሉ በመሆኑ ሥራው በሚፈለገው ደረጃ ማስኬድ አለመቻሉን፣ በተጨማሪም የኢንዱስትሪ መገልገያዎችን አስመልክቶ ከፋብሪካዎቹ ጋር አከራካሪ ጉዳይ ባለመግጠሙ የመገምገም ሥራዎች አለመከናወናቸው ገልጸዋል፡፡

116. በመሆኑም ከፍቃድ ሰጪ አካላት ጋር የሥራ ግንኙነት ባለመኖሩ በአካባቢ ብክለት ለመከላከል አስቀድሞ መሰራት የሚገባቸው ሥራዎች እንዳይሰሩ በማድረግ ለመቆጣጠር የሚደረገውን ጥረት ላይ ክፍተት መፍጠሩ እንዲሁም የመገልገያ መሳሪያዎቹ በሚጠበቀው ደረጃ እና ጥራት ስለመስራታቸው ክትትል ባለመደረጉ

የፋብሪካዎች ዝቃጭ/ቆሻሻ ማከሚያ መሳሪያዎች በትክክል የተሟላ አገልግሎት ስለመስጠታቸው ማረጋገጫ እንዳይኖር አድርጓል፡፡

**ኮሚሽኑ የተቀላጠፈ የመረጃ አያያዝና**

**አጠቃቀም ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ፤**

117. ኮሚሽኑ በፌዴራል ደረጃ የሚከፈቱ ኢንዱስትሪዎች /አምራች ተቋማት/ ለክትትል በሚያመች መልኩ ስለፋብሪካው የተሟላ መረጃ በማሰባሰብ ሊይዝ እና የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

118. በኦዲቱ ወቅት ከኮሚሽኑ ለሥራ ኃላፊዎች ከቀረበ በቃለ-መጠይቅና በተከለሱ ማስረጃዎች መሰረት በኮሚሽኑ በፌዴራል ደረጃ የሚከፈቱ ኢንዱስትሪዎች /አምራች ተቋማት/ ለክትትል በሚያመች መልኩ የተሟላ መረጃ አለመኖሩና የአካባቢ መረጃዎችን ለመሰብሰብ፣ ለማደራጀትና  እና መረጃዎችን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመጠቀም የሚያስችል የአካባቢ መረጃ ሥርዓት አለመዘርጋቱ ለማወቅ ተችሏል፡፡

119. እንዲሁም እስከታችኛው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ያለው አደረጃጀት የተለያየ መሆኑ እና ከላይ እንደተገለጸው የኮሚሽኑ አደረጃጀትም መቀያየር መረጃዎች በአግባቡ እንዳይሰበሰቡ ማድረጉ  ዓመታዊ እቅድ እና የአፈፃፀም ሪፖርትም ላይ በወቅቱ ለማግኘት  ክፍተት መፍጠሩ  እና ዳታ ቤዝ እንዲኖር ድጋፍ ከሚያደርጉ አካላት ጋር መነጋገራቸውንና ለወደፊት በመ/ቤታቸው ሊሰራ ቢታሰብም መ/ቤቱ የራሱ የሆነ ህንፃ የሌለውና በኪራይ ህንፃ ላይ እየሰራ በመሆኑ ሥርዓቱን ለመዘርጋት መቸገራቸውን ገልጸዋል፡፡

120. በመሆኑም ጠንካራ  የኢንፎርሜሽን ሥርዓት ባለመኖሩ ከፍቃድ ሰጪ አካላት፣ ከክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች እስከታችኛው መዋቅር ያለውን መረጃ በቀላሉ እንዳይለዋወጡ ማድረጉ እና እንደሀገር አካባቢ ብክለት በተመለከተ ዝርዝር መረጃዎች ተደራሽ ባለመሆናቸው ችግሮችን  ለበላይ አመራሩ ቀርበው መፍትሄ እንዳያገኙም ያደርጋል፡፡

ፋብሪካዎች ያመነጨቱን በካይ ነገር ያስወገዱበትን መንገድ መረጃ መያዛቸውንና ኮሚሽኑ በኢትዮጵያ የበካይ ነገሮች መጠንን አወጋገድ ዘገባ ማቅረቡን በተመለከተ፤

121. ደንብ ቁጥር 159/2001 የሚመለከተው ማንኛውም ፋብሪካ ያመነጨውን በካይ ነገር ያስወገደበትን መንገድና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን የሚገልጽ መረጃ መዝግቦ ሊይዝ እንዲሁም ኮሚሽኑ የኢትዮጵያ የበካይ ነገሮች መጠንን፣ ምንጭን፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚመለከት ዘገባ ቢያንስ በየአምስት አመቱ ሊያወጣ ይገባል፡፡

122. ብክለትን ለመከላከል የወጣ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 159/2001 መሰረት በናሙና ከታዩት ISO ሰርተፊኬት ካላቸው ጥቂት ፋብሪካዎች(ባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ቢጂአይ ቢራ ፋብሪካ፣ ኮካ ኮላ ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ፣ ኢትዮ ቆዳ ፋብሪካ/ኤጀርሳ)በስተቀር በተቀሩት ፋብሪካዎች ያመነጩትን በካይ ነገር ያስወገዱበትን መንገድና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን የሚገልጽ መረጃ መዝግበው አለመያዛቸው በኦዲቱ ወቅት በመስክ ጉብኝት ወቅት ከፋብሪካዎቹ በተሞሉ መጠይቆችና በኮሚሽኑ በተገኙና ከተከለሱ የክትትል ሪፖርቶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

123. በተጨማሪም በደንቡ መሰረት ኮሚሽኑ የኢትዮጵያ የበካይ ነገሮች መጠንን፣ ምንጭን፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚመለከት ዘገባ ቢያንስ በየአምስት አመቱ ሊያወጣ ይገባል የሚል ቢሆንም ፋብሪካዎች ላይ የተሰራ ዘገባ አለመኖሩን በኦዲቱ ወቅት ከኮሚሽኑ የሥራ ኃላፊዎች በቃ-ለመጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

124. በተጨማሪ ስለጉዳዩ በኮሚሽኑ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና በመውጫ ስብሰባ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በተሰጠ መልስ በ2011 ዓ.ም. በወጣው የአደገኛ ቆሻሻ አዋጅ የበካይ ነገሮችን አመንጫጩት የሚገልጽ በመሆኑ ዘገባው ለመስራት እንደሚረዳቸው ከዚህ በፊት አዋጁ ባለመኖሩ መስራት አለመቻላቸውን ገልጸዋል፡፡

125. ፋብሪካዎች መረጃዎች በአግባቡ አለመያዛቸው መረጃውን በመተንተን ፋብሪካው የደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ ለመቀነስ የተለያዩ ቴክኒኮች እና ቴክኖሎጂዎችን እንዳይተገበር እና የቆሻሻ አወጋገድ ስርዓቱን ደካማ የሚያደርገውና ተቋሙ በህግ የተጣለበትን ግዴታ የሚጥስ በመሆኑ የደረቅ ቆሻሻን መመንጨት ለማስወገድ ወይም ወደተፈላጊው መጠን ለመቀነስ የቆሻሻ መጠን በየጊዜው በመመዝገብ እና ከተመዘገበው መረጃ በመነሳት ለቆሻሻው መመንጨት ምክንያቶችን በመለየት ምክንያቶቹን ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ የሚተገበራቸውን ተግባራት አለመኖራቸውን ያሳያል፡፡

# ክፍል ሦስት

# መደመደሚያ

126. **በመ/ቤቱ የኢንዱስትሪ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ ፖሊሲዎች፣ አዋጆችና ደንቦች እንዲሁም የማስፈፀሚያ መመሪያዎች፣ ማኑዋሎችና ደረጃዎች መዘጋጀታቸውን እና ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ፣**

- በኮሚሽኑ መውጣት ሲገባቸው ያልወጡ መመሪያዎች መኖራቸው (ለመከታተል የሚያስችል የአፈፃፀም መመሪያ፣ ህጉን በማያከብሩ ፋብሪካዎች ለመዝጋት፣ ወደ ሌላ ቦታ ለማዘዋወር የሚያስችል መመሪያ፣ አካባቢ ብክለትን ለመከላከል የሚያስችል ማበረታቻዎች ለመወሰን..) እና የማይተገበሩ መመሪያና ደንቦች መኖራቸው፣
- ለፋብሪካዎች በየጊዜው በሚወጡ ህጎች ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች ቀጣይነት ባለውና ሁሉንም ፋብሪካዎች ባካተተ መልኩ አለመሰጠቱ፣ አዲስ የሚወጡ አዋጆች… የሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁት/እንዲደርሳቸው የተመቻቸ ሁኔታ አለመኖሩና በመ/ቤቱ ድረ-ገጽም አለመጫኑ፣
- በኮሚሽኑ ለአደገኛ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ደረጃ አለመውጣቱ፣ እንዲሁም በኮሚሽኑ ወደ ውሃ አካላትና ወደ ፍሳሽ መቀበያ መስመሮች የሚለቀቁ ፍሳሾች ደረጃዎችን ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ያላወጣ ሲሆን አብዛኛው ፋብሪካዎች ወደ ወንዝ ወይም ወደ ፍሳሽ መስመር የሚለቁት ፍሳሾች አለም አቀፍ ደረጃውን ያሟሉ አለመሆናቸው፣
- በናሙና በታዩት በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ ንግድ ሚኒስቴር በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች፣ በአዳማ፣ በሞጆ፣ በባህርዳር፣ በደሴና ኮምቦልቻ ከተሞች ፍቃድ ሰጪ አካላት (ኢንቨስትመንትና ንግድ ፍቃድ ሰጪ መ/ቤቶች) የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ አዋጁ መሰረት ፋብሪካዎች የኢንቨትመንት ወይም የንግድ ፍቃድ ሲወስዱ የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ እንዲያቀርቡ አለማድረጋቸው እና በተጨማሪም የአካባቢ ብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 159/2001 መሰረት ለማምረቻ ተቋማት የሥራ ፈቃድ ሲሰጡ ልቀቱ በካይ አለመሆኑን፣ ከሆነም

በአካባቢ ደረጃ ከተፈቀደው ጣራ የማይበልጥ እና ልቀቱ ወደ አካባቢ ቢለቀቅ አደጋ የማያስከትል መሆኑን የማረጋገጥ ሥራ የማይሰሩ መሆናቸው፣

- ህንጻ ደንብ ቁጥር 243/2003 መሰረት ህንፃዎች በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ መሰረት ተቀባይነት ያለውን ደረጃ ጠብቀው እንዲሰሩ የሚያስችል የአሰር ሥርዓት አለመዘርጋቱ፡፡

127. **በፌዴራልና በክልል ደረጃ ለሚወገዱ የኢንዱስትሪ ዝቃጭ/ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ ደረጃዎችንና ሕጎችን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ተገቢው የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤**

- በናሙና በታዩት በኮሚሽኑ፣ በአማራና በኦሮሚያ ክልሎች፣ በሰበታ፣ በሞጆ፣ በአዳማ፣ በደሴ፣ ኮምቦልቻና በባህርዳር ከተሞች፣ በደቡብ ወሎ ዞን፣ በተሁሌደረና በሎሜ ወረዳዎች የኢንዱስትሪ ዝቃጮች አካባቢ ላይ የማያደርሱት ጉዳት ለመከታተል በሚያስችል መልኩ በሰው ኃይል፣ በግብዓት(ተሽከርካሪ፣ በቤተ-ሙከራ፣ ካሜራ--አለመኖር) ያልተደራጁ፣ ለመከታተል የሚያስችል የመከታተያ ስልት/አፈፃፀም መመሪያ የሌላቸው እና በከተሞቹ ቀበሌዎች ለፋብሪካዎች ቅርብ እንደመሆናቸው በቀበሌ ደረጃ ያልተደራጁ(ሰበታ፣ አዳማ፣ ሞጆ፣ ደሴና ኮምቦልቻ) በመኖራቸው በኮሚሽኑም ሆነ በናሙና በታዩት በሁሉም የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች መመሪያን መሠረት ያደረገ ጠንካራ የክትትል ሥርዓት አለመኖሩ፣
- ISO" ሰርተፊኬት ለማግኘት ከሚሰሩ ጥቂት ፋብሪካዎች በስተቀር በናሙና ከታዩት አብዛኛው ፋብሪካዎች በኢንዱስትሪ ዝቃጭ አወጋገድ ላይ የወጡ ድንጋጌዎች መከበራቸውን የሚያረጋግጡበት የውስጥ የአካባቢ አያያዝ መቆጣጠሪያ ዘዴ(የአካባቢ በጀት፣ ባለሙያ፣ አሃድ..) የሌላቸውና የአካባቢ የውስጥ ኦዲት የማያስደርጉ ከመሆኑም በላይ ማስደረግ እንዳለባቸውም ግንዛቤው አለመኖሩና የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶችም ፋብሪካዎች ኦዲት እንዲያስደርጉ የማድረግ ሥራው እየተሰራ አለመሆኑ፤ በተጨማሪም ኮሚሽኑን ጨምሮ በሁሉም አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ፋብሪካዎችን ኦዲት የማድረግ ሥራ እየተሰራ አለመሆኑ፣
- በኮሚሽኑ እንደሀገር የሚወገዱ የኢንዱስትሪ ዝቃጮች ወይም ቆሻሻዎች ስለአወጋገዳቸውና በሰው፣ በእንስሳትና በአካባቢ ላይ ስለአደረሱት የጉዳት መጠን ጥናት አለመጠናቱ፣

- ኮሚሽኑ በኢንዱስትሪ ቆሻሻ አወጋገድን ዙሪያ የሚመጡ ቅሬታዎችን ደረጃ በደረጃ ለመፍታት የማያስችል የቅሬታ አቀራረብ እና አፈታት ሥርዓት አለመዘርጋቱ እና የሚመጡ ቅሬታዎች በአዋጁ መሰረት በ90 ቀን ውስጥ መፈታት ቢኖርባቸውም ሳይፈቱ ከሦስት አመት በላይ የሆኑ ቅሬታዎች(የአዲስ አበባና ሞጆ ቆዳ ፋብሪካዎች ላይ የመጣ ቅሬታ) መኖራቸው፣
- የብክለት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 300/1995 ገጽ 61 እና እና ብክለትን ለመከላከል የወጣ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 159/2001 በጤና ወይም በአካባቢ ላይ በሥራ እንቅስቃሴ ሊመጣ የሚችል ጉዳትን ለመከላከል ኮሚሽኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ድርጅትን እስከ መዝጋት ወይም ወደ ሌላ ቦታ እስከ ማዛወር የሚደርስ ማንኛውንም አስፈላጊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል ቢልም በካይ በሆኑ ቆዳ ፋብሪካዎች እና ጨርቃ ጨረቅ ፋብሪካዎች ከማስጠንቀቂያ በዘለለ እርምጃ እየተወሰደባቸው አለመሆኑ፣

128. **መ/ቤቱ ከኢንዱስትሪ ዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ ጋር በተያያዘ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን፣ እንዲሁም የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣**

- ኮሚሽኑ በፌዴራልና በክልል ዘርፉን ለመደገፍ በአዋጁ ኃላፊነት ከተሰጣቸው ተቋማት (ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ ንግድ ሚኒስቴር፣ ኮንስትራክሽን ሚኒስቴርና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና የመሳሰሉት) ጋር ተቀናጅተው መስራት አለመቻሉ እና በኃላፊነት ዘርፉን ያለመደገፍ ሁኔታ መኖሩ፣ በኮሚሽኑና በክልል አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች እስከ ወረዳ ተነባቢ የሆነ ወጥ አደረጃጀት ባለመኖሩ በመ/ቤቶቹ መካከል ጠንካራ የሆነ የሥራ ግንኙነት አለመኖሩ በተጨማሪም በሚፈለገው ደረጃ ኮሚሽኑ ቢሮዎችን አለመደገፉ እና በቅንጅት መሥራት ላይ ክፍተት መኖሩ፣
- በተጨማሪም ከሚመለከታቸው የክልል አካባቢ መ/ቤት እንዲሁም አግባብ ካላቸው ሌሎች መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የኢንዱስትሪ ቆሻሻ ማስወገጃ መገልገያዎችን በመገምገም በአጥጋቢ ሁኔታ መሟላታቸውን የማረጋገጥ ሥራ አለመከናወኑ፣
- ኮሚሽኑ የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ሥርዓት አለመዘርጋቱ፣

- ብክለትን ለመከላከል የወጣ የሚኒስቴሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 159/2001 መሰረት ISO ሰርተፊኬት ካላቸው ጥቂት ፋብሪካዎች/ባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ፣ ቢጂአይ ቢራ ፋብሪካ፣ ኮካ ኮላ ለስላሳ መጠጥ ፋብሪካ፣ ኢትዮ ቆዳ ፋብሪካ/ኤጀርሳ/ በስተቀር በናሙና በታዩት በተቀሩት ፋብሪካዎች ያመነጩትን በካይ ነገር ያስወገዱበትን መንገድና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን የሚገልጽ መረጃ መዝግበው አለመያዛቸው፣
- በደንቡ መሰረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ የበካይ ነገሮች መጠንን፣ ምንጭን፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚመለከት ዘገባ ቢያንስ በየአምስት አመቱ ሊያወጣ ይገባል የሚል ቢሆንም ዘገባው ያልተዘጋጀ መሆኑን፣

# ክፍል አራት

# የማሻሻያ ሐሳቦች

129. **በመ/ቤቱ የኢንዱስትሪ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ ፖሊሲዎች፣ አዋጆችና ደንቦች እንዲሁም የማስፈፀሚያ መመሪያዎች፣ ማኑዋሎችና ደረጃዎች መዘጋጀታቸውን እና ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ፣**

- የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን አዋጅ ብቻ ያላቸውን ህጎች ለአፈፃፀም ይረዳ ዘንድ ደንብና የአፈፃፀም መመሪያዎችን በዘርፉ ካሉ መ/ቤቶች ጋር በመወያየት ሊያወጣ ይገባል፡፡
- ፋብሪካዎች ኢንዱስትሪ ከሚወጡ ዝቃጮች አካባቢያቸውን ለመከላከል እንዲያስችላቸው በየጊዜው በሚወጡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ቀጣይነት ባለው መልኩ በሚመለከታቸው የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች ስልጠናውን እንዲያገኙ ሊያደርግ እና የሚወጡ ህጎችን አውቀው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተለያዩ ሚዲያዎችን እና የመ/ቤቱ ድረ-ገጽ ሊጠቀም ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ በኢንዱስትሪ ዝቃጭ አወጋገድ በአካባቢ፣ በሰው እና በእንስሳ ጤና ላይ ሊመጡ የሚችሉ ጉዳቶችን ከወዲሁ ለመከላከል እንዲያስችል ከደረጃዎች መዳቢ ወይም ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በመካከር ለኢንዱስትሪ የቆሻሻ ዓይነቶች(ጠጣርና ፈሳሽ) አመነጫጨት፣ አያያዝ፣ አከመቻቸት፣ አመካከን፣ አጓጓዝና አወጋገድ ደረጃዎች እንዲወጣ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ወደ ፍሳሽና ወደ ወንዝ የሚለቀቁ ፍሳሽ የሚለቀቁ የፍሳሽ ቆሻሻ ፋብሪካዎች በአገር አቀፍ ደረጃ የወጣ ቢሆንም አብዛኛው ፋብሪካዎች ለመገንባት የግንባታ እቃዎችና ለማከም ኬሚካሎች ውድ መሆናቸውንና የውጭ ምንዛሪ እጥረትን እንደምክንያት የሚያነሱት በመሆኑ እቃዎቹ ከቀረጥ ነፃ የሚገቡበትን ወይም ኬሚካሎችን መንግስት አምጥቶ የሚያከፋፍልበትን መንገድ እንዲያመቻች መ/ቤቱ ከማመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ሊሰራ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ሞጆ ላይ የተጠናውን የጋራ የፍሳሽ ማከሚያ (common treatmen plant)

ከሚመለከታቸው አካላት ጋር (ከመሬት አስተዳደር..)በመነጋገር ተግባራዊ ሊያደርገው ይገባል፡፡

- ኮሚሽኑ ከፍቃድ ሰጪ አካላት ጋር በመነጋገር/በመወያየት ፋብሪካዎች በኢንዱስትሪ ዝቃጭ/ቆሻሻ አወጋገድ ምክንያት ሊያደርሱ የሚችሉትን ጉዳት ግንዛቤውን በመፍጠር ፋብሪካዎች ፍቃድ ሲያወጡ(የኢንቨስትመንትና የንግድ ፍቃድ ሲያወጡ) የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ/የይሁንታ ፍቃድ እንዲያቀርቡ ሊያስደርግ ይገባል፡፡
- የአካባቢ አያያዝ እቅድ እንዲኖራቸው በየደረጃው ያሉ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ያላቸውንና የሌላቸውን ነባር ፋብሪካዎች የመለየት ሥራ አቅደው እንዲተገብሩት በማድረግ ሁሉም ፋብሪካዎች የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት እንዲዘረጉ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሥራ ፈቃድ ከሚሰጡ አካላት ጋር በመወያየት ፍቃድ ከመስጠታቸው በፊት ልቀቱ በካይ አለመሆኑን እና ልቀቱ ወደ አካባቢ ቢለቀቅ አደጋ የማያስከትል መሆኑ የማረጋገጥ ሥራውን በጋራ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ ከኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ጋር በመወያየት በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማው መሰረት የቆሻሻ ማስወገጃው ፋብሪካዎች ከመገንባታቸው በፊት በዲዛይን የሚካተትበትንና ከግንባታውም በኋላ ደረጃውን ጠብቀው ስለመገንባታቸው በባለሙያዎች የሚረጋገጥበትን ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡

130. **በፌዴራልና በክልል ደረጃ ለሚወገዱ የኢንዱስትሪ ዝቃጭ/ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ ደረጃዎችንና ሕጎችን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ተገቢው የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፤**

- ኮሚሽኑ እንደሀገር ፋብሪካዎች በምርት ሂደት ወቅት ስለሚያመነጩት ቆሻሻዎች አወጋገድና እስካሁን በተጨባጭ ያደረሱትን የጉዳት መጠን ለማወቅ እንዲያስችል እና በሁሉም ትኩረት ተሰጥቶ ለመስራት ያስችል ዘንድ እስካሁን ያደረሱትን ጉዳት በማጥናት ለሚመለከተው አካላት በሙሉ ሊያሳውቅ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ በተለይ በፌዴራል ደረጃ ፍቃድ የሚያወጡ ኢንዱስትሪዎች ቆሻሻ አወጋገድ ዙሪያ ያለውን የክትትል ሥርዓት ምን መምሰል /በምን ያህል ጊዜ፣ በማን እና እንዴት/እንዳለበት የሚገልጽ የአፈፃፀም መመሪያ በማውጣትና በፌዴራል ደረጃ ፈቃድ የሚያወጡ እና ክልል ተሻጋሪ ፋብሪካዎች በሚቋቋሙበት

አካባቢ ለሚገኝ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ለክትትል እንዲመች የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ ሊልኩ ይገባል፡፡

- ኮምሽኑ ፋብሪካዎች በሚቀርበው የአካባቢ ተጽእኖ ግምገማ ሰነድ መሰረት መተግበራቸውን እና አካባቢ ብክለትን ለመከላከል በሚወጡ ህጎችና ደረጃዎችን ስለመተግበራቸው ለመከታተል ያስችለው ዘንድ የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶችን እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ ወጥና ተነባቢ የሆነ አወቃቀር እንዲኖራቸው በማድረግ እና በሰው ኃይልና በግብዓት እንዲደራጁ የመደገፍ ሥራ በመስራት የክትትል ሥራውን ሊያጠናክርና ሁሉም ፋብሪካዎች የአካባቢ አያያዝ ሥርዓት እንዲዘረጉ በማድረግ የብክለት መጠናቸው እንዲቀንሱ ሊያደርግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ኮሚሽኑ በፌዴራል ፍቃድ የሚያወጡ ድርጅቶች የሚያሰሩትን የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሰነድ ለክትትል ያመች ዘንድ ድርጅቱ በሚቋቋምበት ክልል/ከተማ አስተዳደር ሊልክ ይገባል፡፡
- በኢንዱስትሪ ዝቃጭ/ቆሻሻ አወጋገድ ላይ የወጡ ህጎችን የማያከብሩ ፋብካዎችን ቀጣይ የሆነ ክትትል ስርዓት በመዘርጋትና በወቅቱ ግብረ መልስ በመስጠት ማስተካከያ በማያደርጉት ላይ በአዋጁና በደንቡ መሰረት እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ ፋብሪካዎች ኦዲት ማስደረግ እና ለሚመለከታቸው አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች መላክ እንዳለባቸው ግንዛቤው በመስጠት በሁሉም የአካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች እንዲልኩ ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ኮሚሽኑ በራሱም እንዲሁም በክልልና በከተሞች የሚገኙ አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶችም የተጀመረውን የአካባቢ ኦዲት ማንዋል በማጠናቀቅ በእቅዳቸው አካተው እንዲሰሩ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ ችግሮች በተዋረድ ወይም ደረጃ በደረጃ የሚፈቱበትን የክልል ተሻጋሪ ፋብሪካዎችን ጨምሮ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ በጋራ የሚፈቱበት ወጥ የሆነ የቅሬታ አቀራረብ መመሪያ አውጥቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ ባለሀብቶች ተጠያቂነት እንዲሰማቸው በብክለት አዋጁ እርምጃ አወሳሰዱ ምን መሆን እንዳለበት በዝርዝር የሚገልጽ መመሪያ በማውጣትና ባለሀብቶችና የፍትህ አካላት ግንዛቤውን በመስጠት እርምጃውን ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

131. **መ/ቤቱ ከኢንዱስትሪ ዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ ጋር በተያያዘ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን፣ እንዲሁም የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ሥርዓት መዘርጋቱን በተመለከተ፣**

- ኮሚሽኑም ሥራውን በጥራት በአግባቡ ለመሥራት እንዲያስችለው ከባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ የሚሰሩበት የጋራ እቅድ በማቀድ እና በአካባቢ ላይ የሚደርሱ ችግሮች ለይቶ የሚፈታበት ከባለድርሻ አካላት ጋር ወጥ የሆነ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ጠንካራ የሆነ የሥራ ግንኙነት በመፍጠር የተቀናጀ ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡
- ኮሚሽኑ ከሚመለከታቸው የክልል አካባቢ መ/ቤት እንዲሁም አግባብ ካላቸው ሌሎች መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የኢንዱስትር ቆሻሻ ማስወገጃ መገልገያዎችን በአግባቡ እንደሚሰሩ በመገምገምና በአጥጋቢ ሁኔታ መሟላታቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
- በየጊዜው የሚቋቋሙ ፋብሪካዎችን የኢንቨስትመንት/ንግድ ፈቃድ ከሚሰጡ አካላት ጋር በመተባበር ለክትትል ያመቸው ዘንድ ፕሮጀክቶች በትክክል ያሉበትን ቦታ እና ሁኔታ የተሟላ መረጃ በማሰባሰብ በማዕከል ሊይዝ ይገባል፡፡
- በኮሚሽኑ አካባቢ ብክለት ዙሪያ ያሉ መረጃዎች በቀላሉ ለማግኘትና /መረጃዎችን online/ በቀላልና በቅልጥፍናና ሥራዎችን በጥራት ለመሥራት የሚያስችል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ የበካይ ነገሮች መጠንን፣ ምንጭን፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚመለከት ዘገባ የሚወክል የፋብሪካዎችን ቁጥር በናሙና በመምረት ቢያንስ በየአምስት አመቱ ሊያወጣ ይገባል፡፡

# አባሪ አንድ

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

**ኦዲት አካባቢ፣ የኢንዱስትሪ ቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት ውጤታማነትን በተመለከተ**

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች /Audit Issue/ | የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/ | አስተያየት /Comment/ |
|---|---|---|
| 1. በመ/ቤቱ የኢንዱስትሪ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ ፖሊሲዎች፣ አዋጆችና ደንቦች እንዲሁም የማስፈፀሚያ መመሪያዎች፣ ማኑዋሎችና ደረጃዎች ስለመዘጋጀታቸውና ተግባራዊ መደረጋቸውን በተመለከተ፣ | 1.1 ኮሚሽኑ ከኢንዱስትሪ ዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ ጋር በተያያዘ የወጡ አዋጆችን እና ደንቦችን መሰረት በማድረግ መመሪያ ሊያወጣ እና ተግባራዊ ሊደርጉ ይገባል፡፡ | |
| | 1.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በስራ ላይ የሚገኘውን የአካባቢ ፖሊሲ ሰነድ ከፌደራል እና ከክልል የዘርፍ መ/ቤቶች፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና በአካባቢ ላይ ከሚሰሩ አጋር ድርጅቶች እንዲሁም ሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የውጪ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ለመስራት የሚያግዝ የአካባቢ ፖሊሲ ጸድቆ እንዲወጣና ተግባራዊ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡ | |

| | | |
|---|---|---|
| | 1.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ አግባባ ካላቸው መ/ቤቶች ጋር በመካከር ለተለያዩ የቆሻሻ ዓይነቶች አመነጫጨት፣ አያያዝ አከመቻቸት፣ አመካከን፣ አጓጓዝና አወጋገድ የሚያገለግሉ የመጠንና የአተገባበር ደረጃዎች ሊያወጣ ይገባል፣ | |
| | 1.4 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወደ ውሃ አካላትና ወደ ፍሳሽ መቀበያ መስመሮች የሚለቀቁ ፍሳሾች ደረጃዎችን ሊያወጣ ይገባል፡፡ | |
| | 1.5 ከኢንዱስትሪዎች ወይም ከፋብሪካዎች የሚወጡ ዝቃጭ ብክለት እንዳያስከትል የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሊዘጋጅና ግምገማው በሚመለከተው አካል መጽደቅ ይኖርበታል፡፡ | |
| | 1.6 በኢንዱስትሪዎች የሚገነባ የዝቃጭ ማስወገጃ ወይም ማከሚያ ግንባታ በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ መሠረትና ተቀባይነት ያለውን ደረጃ ተከትሎ የተሰራ ስለመሆኑ አገልገሎት ከመስጠቱ በፊት በሚመለከተው አካል መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ | |
| | 1.7 ለማምረቻ ተቋማት ሥልጣን የተሰጠው ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት የሥራ ፈቃድ የሚሰጠው ልቀቱ በካይ አለመሆኑን፣ ከሆነም በአካባቢ ደረጃ ከተፈቀደው ጣራ የማይበልጥ እና ልቀቱ ወደ አካባቢ ቢለቀቅ አደጋ የማያስከትል መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ሊሆን ይገባል | |
| | 1.8 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማንኛውም ሰው ፈቃድ ሳይሰጠው የኢንዱስትሪ ዝቃጭ ያዘለ ፈሳሽ ወይም ጠጣር ነገር ወደ ማንኛውም ፍሳሽ መቀበያ፣ ወንዝ፣ ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ እንዳይለቀቅ ወይም እንዳይጣል ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ | |
| | 1.9 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢንዱስትሪ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድን በተመለከተ በወጡ ፖሊሲዎች፣ ደረጃዎች፣ አዋጆችና ደንቦች ላይ ለአምራች ድርጅቶች ግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሰጥ ይገባል፡፡ | |

| | | |
|---|---|---|
| | 1.10 የኢንዱስትሪ ዝቃጭ/ ብክለት አወጋገድን በተመለከተ ሚ/መ/ቤቱ ያወጣቸውን ፖለሲ የአካባቢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ለሁሉም አምራች ተቋማት /ፋብሪካዎች/ የሚደርሰበትን መንገድ ሊያመቻች ይገባል፡፡ | |
| 2. በፌዴራልና በክልል ደረጃ ለሚወገዱ የኢንዱስትሪ ዝቃጭ/ቆሻሻዎች አያያዝና አወጋገድ ደረጃዎችንና ሕጎችን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ተገቢው የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓት መዘርጋቱን ማጣራት፣ | 2.1 በሚኒስቴር መ/ቤቱ እንደሀገር በፌዴራልም ሆነ በክልል የሚወገዱ የኢንዱስትሪ ዝቃጮች ወይም ቆሻሻዎች ስለአወጋገዳቸውና ስለአስከተሉት/ስለሚያስከትሉት የጉዳት መጠን ጥናት ሊያጠና ይገባል፡፡ | |
| | 2.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በኢንዱስትሪ ቆሻሻ አወጋገድ ዙሪያ የክትትል ሥርዓት ሊዘረጋና ተግባራዊ ሊያደርግበት የሚያስችል የአፈፃፀም መመሪያ ሊኖረው ይገባል፡፡ | |
| | 2.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ፋብሪካዎች በኢንዱስትሪ ዝቃጭ አወጋገድ ላይ የወጡ ድንጋጌዎች መከበራቸውን የሚያረጋግጡበትን የውስጥ የአካባቢ አያያዝ መቆጣጠሪያ ዘዴ አዘጋጅተው መተግበራቸውን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ | |
| | 2.4 ሚኒስትር መ/ቤቱ የኢንዱስትሪ ቆሻሻ ዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ ላይ የወጡ ህጎች ተግባራዊነት ለመከታተል የድርጊት መርሐ ግብር/action paln/ በማዘጋጀት ወቅታዊ የሆነ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡ | |
| | 2.5 ማንኛውም ነባር ፋብሪካ በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ መሰረት የአካባቢ ኦዲት ሊያደርግና ሪፖርቱን ለሚመለከተው ተቆጣጣሪ አካል ሊልክ ይገባል፡፡ | |

| | | |
|---|---|---|
| | 2.6 መ/ቤቱ የኢንዱስትሪ ቆሻሻ አወጋገድን የቅሬታና አቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ | |
| | 2.7 በጤና ወይም በአካባቢ ላይ አደጋ እንዳያስከትል ከሚያሰጋ የሥራ እንቅስቃሴ ሊመጣ የሚችል ጉዳትን ለመከላከል ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ድርጅትን እስከ መዝጋት ወይም ወደ ሌላ ቦታ እስከ ማዛወር የሚደርስ ማንኛውንም አስፈላጊ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡ | |
| 3. **መ/ቤቱ ከኢንዱስትሪ ዝቃጭ አያያዝና አወጋገድ ጋር በተያያዘ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት ለመስራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን፣ እንዲሁም የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ሥርዓት መዘርጋቱን ማረጋገጥ፤** | 3.1 **ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ የሥራ ግንኙነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፡፡** | |
| | 3.1.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወጥ አደረጃጀት ለመፍጠርና ቅንጅታዊ አሰራርን ለማጠናከር ከክልሎችና ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር ድጋፍ ለማድረግ እቅድ በማውጣት በቅርበት ሊሰራ ይገባል፡፡ | |

| | | |
|---|---|---|
| | 3.1.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ በፌዴራል ደረጃ የሚከፈቱ ኢንዱስትሪዎች /አምራች ተቋማት/ ለክትትል በሚያመች መልኩ ስለፋብሪካው የተሟላ መረጃ በማሰባሰብ ሊይዝ ይገባል፡፡ | |
| | 3.1.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው የክልል አካባቢ መ/ቤት እንዲሁም አግባብ ካላቸው ሌሎች መ/ቤቶች ጋር በመተባበር የኢንዱስትር ቆሻሻ ማስወገጃ መገልገያዎችን መገምገምና በአጥጋቢ ሁኔታ መሟላታቸውን በማረጋገጥ አስፈላጊው እርምጃዎችን ሊወስድ ይገባል፡፡ | |
| | **3.2 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ዘመናዊና ቀልጣፋ የመረጃ አያያዝና ልውውጥ ሥርዓት የዘረጋና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፡፡** | |
| | 3.2.1 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የአካባቢ መረጃ አሰባሰብን፣ አደረጃጀትን እና አጠቃቀምን የሚያቀላጥፍ የአካባቢ መረጃ ሥርዓት ሊዘረጋ ይገባል፡፡ | |
| | 3.2.2 ደንብ ቁጥር 159/2001 የሚመለከተው ማንኛውም ፋብሪካ ያመነጨውን በካይ ነገር ያስወገደበትን መንገድና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮችን የሚገልጽ መረጃ መዝግቦ ሊይዝ ይገባል፡፡ | |
| | 3.2.3 ሚኒስቴር መ/ቤቱ ማንኛውም ፋብሪካ የደንብ ቁጥር 159/2001 ድንጋጌዎች እንዴት እየተገበረ እንደሆነ የሚገልጽ ስልጣን ለተሰጠው የአካባቢ መ/ቤት በየዓመቱ መረጃ እንዲያቀርቡ ሊያደርግ ይገባል፡፡ | |
| | 3.2.4 ሚኒስቴር መ/ቤቱ የኢትዮጵያ የበካይ ነገሮች መጠንን፣ ምንጭን፣ ዝውውርንና አወጋገድን የሚመለከት ዘገባ ቢያንስ በየአምስት አመቱ ሊያወጣ ይገባል፡፡ | |

አባሪ 2

# በምርት ሂደት ወቅት ከፋብሪካዎች የሚወጡ የፍሳሽ ቆሻሻ ደረጃዎች

# STANDARDS FOR INDUSTRIAL SECTORS